# ፍለጋ

የእግዚአብሔርን ቃል፣ የእግዚአብሔርን ዓለም እና የእግዚአብሔርን ሥራ

## እንወቅ



# ፍለጋ

የእግዚአብሔርን ቃል  የእግዚአብሔርን ዓለም እና የእግዚአብሔርን ሥራ

## እንወቅ

ፍለጋ

የቅጂ መብት 2014 የሚሽን ማስተባበሪያ ማዕከል

በሲኤምኤም አሳታሚ የታተመ

cmmpress.org

ሁለተኛ እትም ሶስተኛ እትም 2014.

የአሳታሚው መብቶች በሕግ የተጠበቁ ናቸው፡፡

ፍለጋ የተባለው ይህ ጽሑፍ የሚሽን ማስተባበሪያ ማዕከል ንብረት ነው፡፡ mobilization.org

በዓለም ዙሪያ ያሉ በሥራው የተሳተፉትን ሁሉ በሚያከብር መልኩ ይህንን ጽሑፍ በተቻለ መጠን ብዙዎች እንዲጠቀሙበት ለማድረግ ምኞታችን ነው፡፡ ይህንን ጽሑፍ ለመተርጎምም ሆነ፣ ለእናንተ ባህል ዓውዳዊ በሆነ መልኩ ለመጠቀም የምትፈልጉ ከሆነ ከእናንተ ጋር ተባብረን ለመሥራት ዝግጁ ነን፡፡ ለትርጉም የሚረዳ መምሪያ በሚከተለው ድረ ገጽ ላይ ይገኛል፡፡ mobilization.org/translation

በሚከተለው አድራሻ ልታገኙን ትችላላችሁ resources@mobilization.org.

Unless otherwise indicated, all Scripture quotations are from The Holy Bible, English Standard Version, copyright © 2001 by Crossway Bibles, a division of Good News Publishers.
Used by permission. All rights reserved.

First Edition, Second Imprint, 2016.
C: 06-06-16   M: 12-15-16 2:45

# ማውጫ


ትምህርት 1 የእግዚአብሔር ቃል፡- የእግዚአብሔር ልብ........................... 3

ትምህርት 2 የእግዚአብሔር ዓለም፡- ሐሙጎቡሒ..................................... 11

ትምህርት 3 የእግዚአብሔር ሥራ፡- መጸለይ............................................. 19

ትምህርት 4 የእግዚአብሔር ሥራ፡- መላክ................................................. 27

ትምህርት 5 የእግዚአብሔር ሥራ፡- መቀበል............................................ 35

ትምህርት 6 የእግዚአብሔር ሥራ፡- መሔድ.............................................. 43

ትምህርት 7 የእግዚአብሔር ሥራ፡- ማስተባበር........................................ 51

ተቀጥላ እና ጠቃሚ ጽሑፎች........................................................................ 64



# መግቢያ

## እንደዚህ አስባችሁ ታውቃላችሁ?

- መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረው ስለምንድን ነው?
- እግዚአብሔር በዓለም ላይ አሁንም እየሠራ ነው?
- ሕይወቴ የአንድ የሌላ ትልቅ አካል ክፍል እንዲሆን ይፈለጋልን?

## ፍሊጋ ስለምን ይናገራል?

- እግዚአብሔር ለአብርሃም ስለ ሰጠው ተስፋ ነው፡፡
- ስለ ኢየሱስ መከራ ነው፡፡
- ስለቤተክርስቲያን ዓላማ ነው፡፡
- በዓለም ዙሪያ ሁሉ በፍጥነት በማደግ ላይ ስላለው ንቅናቄ ነው፡፡

ስለ ዋናው የእግዚአብሔር ልብ ነው :- ውሃ ባህርን እንደሚከድን እንዲሁ ምድር ሁሉ እርሱን በማወቅ በክብሩ ትሞላ ዘንድ ስለሚያስበው ልቡ (እንባ 2፡14) ፡፡

## ፍሊጋን መጀመር!

ይህ ጥናት የተዘጋጀው የእግዚእብሔርን ቃል፣ የእግዚአብሔርን ዓለምና፣ የእግዚአብሔርን ሥራ ለመፈለግና ለማጥናት ነው፡ ፡ ስለዚህም አንዳንድ ወዳጆቻችሁን አሰባስቡና በዚህ የጥናት ጉዞ ውስጥ የምትማሩትን ነገር ተወያዩበት፡፡

### በእያንዳንዱ ትምህርት ውስጥ የተካተቱት የሚከተሉት ናቸው፡፡

| | |
|---|---|
| ዝግጅት | ስለ እግዚአብሔር ቃል፣ ዓለም፣ እና ሥራ ያላችሁን አመለካከት መዝኑ፡፡ |
| አንብቡ | እግዚአብሔር ምን እየሠራ እንዳለና ከእርሱም ጋር እንዴት መሥራት እንደምትችሉ ጠቃሚ ትምህርትን ቅሰሙ፡፡ |
| ተወያዩ | በእነዚህ ጥያቄዎች ተዘጋጁ፤ ጥቅሶቹን አጥኑ፣በፍሊጋ የጥናት ቡድናችሁ የውይይት ጊዜ ሃሳባችሁን አካፍሉ |
| በህይወት ኑሩት | ጽኑ እምነቶችቻችሁን በህይወት እንድትኖሯቸው አዳዲስ  መንገዶችን መርምሩ፡፡ |
| ጸልዩ | ወደ እግዚአብሔር ሃልዎት በመግባት ኢየሱስን ስለማያውቁና እርሡን ወደ መውደድ ስላልደረሱ ሕዝቦች ማልዱ፡፡ |



# ትምህርት 1
# የእግዚአብሔር ቃል: የእግዚአብሔር ልብ

ለእግዚአብሔር ዓላማ ከመስራት ይልቅ ሌላ አንድ የሆነ ነገር መስራት ትችላላችሁ፤ ነገር ግን ይህ ሁል ጊዜ ያነሠ ይሆናል፣ እናም ከሌላ ከተሻለና ከላቀ ነገር ጋር መምጣት አትችሉም፡፡ ስትቨ ሀውቶርን

## ዝግጅት

### ከዘፍጥረት እስከ ራዕይ

መጽሐፍ ቅዱስን በልጅነታችን ስንማር ብዙዎቻችን አንድን ታሪክ በአንድ ጊዜ በማጥናትና ታሪኩን በቀጥታ ከግል ሕይወታችን ጋር በማዛመድ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን የምትመለከቱት እና የምታነቡት እንዴት ነው?

1. **የሕግ መጽሐፍ፡-** ምን ማድረግ እንዳለብኝ ይነግረኛል፤ ማድረግ የሌለብኝንም ያስጠነቅቀኛል፡፡
2. **መንፈሳዊ ጥበቃ፡-** በየዕለቱ አንድ ቃል ዲያቢሎስን ያርቃል፡፡
3. **የመስታወት ኳስ፡-** እግዚአብሔር ለወደፊት ህይወቴ ያለውን ዕቅድ፣ ስለ ትዳር ጓደኛ፣ ስለሥራ፣ ወዘተ እንዳውቅ ይረዳኛል፡፡
4. **መንፈሳዊ ቡና፡-** እንድነቃ ይረዳኛል፣ ቀኑንም በመልካም ያስጀምረኛል፡፡
5. **የቤተሰብ ሐኪም፡-** መልካም ስሜት እንዲሰማኝ ስፈልግ ወደ መፅሐፉ እዞራለሁ፡፡
6. **ወደ ሐብት የሚያደርስ ካርታ፡-** እግዚአብሔር በጤናና በሐብት እንደሚባርከኝ የተስፋ ቃሉን ይገልጥልኛል፡፡

እነዚህ ከላይ የቀረቡት ሁሉ መጥፎ አመለካከቶች አይደሉም፤ ነገር ግን የዚህ አመለካከት ውጤቱ ብዙዎቻችን መጽሐፍ ቅዱስን የጋራ መሪ ሀሳብና ዓላማ የሌላው የተነጣጠሉ መንፈሳዊ ታሪኮች ስብስብ እንደሆነ አድርገን እንድናየው ማድረጉ ነው፡፡ እውነታው ግን መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እኛ ከመናገር ይልቅ በአብዛኛው ስለ እግዚአብሔርና እርሱ በህዝቦች ሁሉ ለመመለክ ስላለው ናፍቆት የሚናገር ነው፡፡

እግዚአብሔር በምድር ላይ ባሉ ሕዝቦች ሁሉ እንዲከብር ያለውን ናፍቆት የሚናገሩ ከ1,600 የሚበልጡ ጥቅሶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አሉ፡፡ ይህ ትምህርት ከእነዚህ ጥቅሶች መካከል ጥቂቶቹን ያሣያል፡፡ (ለተጨማሪ ጥቅሶች በገጽ 59 ላይ የቀረቡትን ዝግጅቶች ተመልከት፡፡

---

### [ሕዝቦች]

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይህ ቃል አብዛኛውን ጊዜ ብሔርና ብሔረሰቦችን የሚመለክት ነው፡፡ ሕዝቦች ወይም አሕዛብ የሚሉት ቃላትም እንዲሁ ተመሳሳይ ሃሳብን ለማስተላለፍ ተጠቅሞባቸዋል፡፡

### [ዓለም አቀፍ ክርስቲያኖች]

እግዚአብሔር ለዓለም ያለውን የልቡን ሃሳብ የተገነዘቡ በየትም ስፍራ ቢኖሩና ምንም ዓይነት ስራ ቢሠሩ፣ እግዚአብሔር በሕዝቦች መካከል ከብሮ ለማየት ሕይወታቸውን ስልታዊ በሆነ መንገድ ይኖራሉ ደግሞም ይሠራሉ፡፡

# የእግዚአብሔር ልብ ለዚህ ዓለም

በቶድ አህረንድ

ሚሽን የሚለውን ቃል ስታስቡ የትኛው ጥቅስ ወደ አእምሮአችሁ  ይመጣል? ብዙዎቻችን የፈለግነውን ያህል አእምሮአችንን ብንጨምቀው ከታላቁ ተልዕኮ ያለፈ መጥቀስ አንችልም፡፡ ለዓመታት የቤተክርስቲያናችን ባህል እንደሚያሳየው፡ የሚሽን ኮንፈረንሶቻችን መሪ ኃሳብና፡ ተልከው ለሚሔዱ ሰዎች ተነሳሽነትን ለመፍጠር የምንጠቀመው ይህንኑ ቃል ነው፡፡ ነገሩን ሁሉ በአንድ ጥቅስ ላይ ለምናንጠለጥለው ለእኛ ታዛዥነታችን አዝጋሚ ቢሆን አያስደንቅም፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ ከታላቁ ተልዕኮ ባለፈ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የሚናገረው ብዙ ነገር አለው፡፡ የሚሽንን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ልንረዳ ያስፈልገናል፡፡ ምናልባትም “ለሚሽን መሠረት የሚሆን አንድ ምንባብ ማግኘት ይቻላል?” ብላችሁ ትጠይቁ ይሆናል፡፡ አዎ!  በእርግጥ እግዚአብሔር ምድርን በክብር ለመሸፍን ያለው ናፍቆት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባሉ በእያንዳንዱ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኝ ነው፡፡ ስድሳ ስድስቱም መጻሕፍት ወደ አንድ መሪ ሃሳብ ሊጠቃለሉ የማይችሉ ከመሰላችሁ ማንበባችሁን ቀጥሉ፡፡ ሚሽን የመጋቢያችሁ፣ የካምፓስ አገልጋያችሁ ወይም ደግሞ የአንተ (ቺ) ሃሳብ ሳይሆን፣ የእግዚአብሔር ሃሳብ እንደሆነ ትገነዘባለህ(ቢያለሽ)፡፡ እግዚአብሔር ከፍጥረት ጀምሮ  ሕዝቦችን ሁሉ ወደ ራሱ ለመዋጀት ይፈልጋል፡፡

እንደ ክርስቲያን እግዚአብሔር ዓለምን እንደሚያይ ማየታችን በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን እግዚአብሔር ለዓለም ካለው ልብ አንጻር ስንመለከት ከዘፍጥረት ጀምሮ እስከ ራዕይ ድረስ፡ እናንተን፣ እኔንና፣ የእርሱ የሆነውን ሕዝብ ሁሉ ከእርሡ ጋር ሆነን የቀረውን እያንዳንዱን ሕዝብ ወደ ዙፋኑ እንድናመጣ ሲጣራ እናገኘዋለን፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ምንም የጋራ የሆነ መሪ ሃሳብ ወይም የጋራ ታሪክ የሌላቸው መጻሕፍት ስብስብ ሳይሆን ፡ አንድ መሪ ሐሳብ ያለው አንድ ወጥ መጽሐፍ ነው፡፡ስብስብ ሳይሆን ፡ አንድ መሪ ሐሳብ ያለው አንድ ወጥ መጽሐፍ ነው፡፡



# ተወያዩ

## የእግዚአብሔር ዓለም አቀፋዊ ናፍቆትና ዓላማ

### [ጠቅላላ እይታ]

የፍፃሜ ስዕል - ራዕይ 7፡9-10
መሠረታዊ ተስፋ - ዘፍ 12፡1-3 እና ገላ 3፡8
አስደናቂ መዋጀት ራዕይ 5፡9-10

1. እነዚህ ጥቅሶች ስለ እግዚአብሔር አጠቃላይ ዓላማና ናፍቆት ምን ያስተምራሉ ?

2. እግዚአብሔር ለአብራም (በኋላ አብርሃም ተብሎ ለተጠራው) ምን ተስፋ እንደሰጠው፣ እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለዘሩ ስላሰበላቸው ሀሳብ፡ እና ጳውሎስ ስለወንጌል ያለውን መረዳት ተወያዩባቸው፡፡

2. እነዚህ ጥቅሶች እንዴት ያነሳሱናል እና ያበረታቱናል?

# [ብሉይ ኪዳን]

*ምንም እንኳን ብሉይ ኪዳን በቀዳሚነት ስለ እስራኤል የሚናገር ቢሆንም፣ እግዚአብሔር ለአሕዛብ ሁሉ ያለውን ልብና ለእነርሱም ያነበረውን ፍላጎት በሚናገሩ ጥቅሶች የተሞላ ነው፡፡*

1. 1ኛ ሳሙኤል 17፡45-47
   ዳዊት ጎልያድን ለመገዳደር የገፋፋው ሀሳብ ምን ነበር?

2. 1ኛ ነገሥት 8፡41-43
   ሰለሞን መቅደሱን ለጌታ ለመስጠት ሲጸልይ ስለእግዚአብሔር ዝናና ምኞት እንግዳ ከሆኑ ሰዎች የሚጠብቀው ምን ነበር?

3. ዳንኤል 6፡25-27
   ዳንኤል ለእግዚአብሔር ያለው ፍጹም መሰጠት ከአንበሶች አፍ ከተረፈ በኋላ ምን ውጤት አስገኘ?

4. ዘጸአት 19፡6
   እስራኤላውያን ስለመሲሁ መምጣት የሚያስቡት ለእነርሱ እና ለእነርሱ ጥቅም ብቻ እንደሚመጣ ነበር፤ ነገር ግን እነዚህ ጥቅሶች ምን ያስተምሩናል?

5. መዝሙር 46፡10
   የዚህን ጥቅስ የመጀመሪያ ግማሽ ክፍል ብዙዎች ያውቁታል፤ የመጨረሻውን ግማሽ ግን አያውቁትም፡፡ በዙሪያችን ያለው ሁኔታ ሲመሰቃቀል የጥቅሱ ሁለቱም ክፍሎች ምን ዓይነት ዋስትና ይሰጡናል?

6. መዝሙር 67
   የመዝሙር መፅሐፍ አንድ ሶስተኛው ክፍል ስለ ሕዝቦች እና እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ስላለው ግንኙነት ይናገራል፡፡ በዚህ ምሳሌ ውስጥ ለአንተ ወይም ለአንቺ የተለየ ትርጉም ያለው የትኛው ነው?

7. ኢሳይያስ 25፡6-8
ለሚያምኑ ሁሉ እግዚአብሔር እንዲሆንላቸው ያሰበው ምንድን ነው?

8. ኢሳይያስ 49፡6 እና ሉቃስ 2፡25-32
እስራኤላውያን ስለመሲሁ መምጣት  የሚያስቡት ለእነርሱ እና ለእነርሱ ጥቅም ብቻ እንደሚመጣ ነበር፤ ነገር ግን እነዚህ ጥቅሶች  ምን ያስተምሩናል?

## [አዲስ ኪዳን]

1. ዮሐንስ 4፡35፣ ማርቆስ 11፡15-17፣ ማቴዎስ 24፡14  በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ ኢየሱስ ስለ ሕዝቦች ምን አስተማረ?
ማቴዎስ 28፡18-20 (በተጨማሪም ማርቆስ 16፡15፣ ሉቃስ 24፡45-47፣ ዮሐንስ 20፡21 እና ሐዋ 1፡8 ተመልከቱ።)
በእነዚህ ጥቅሶች መሠረት ክርስቲያኖች የተሰጣቸው ተልዕኮ ምንድን ነው? ይህስ እግዚአብሔር ካለው ዓለም አቀፋዊ ናፍቆት ጋር እንዴት ይገናኛል?

2. ሐዋ 17፡26-27
ባለፉት ታሪኮች ሁሉ ውስጥ እግዚአብሔር ለሰዎች ሁሉ ስለነበረው ፍላጎትና በመካከላአው ስለሠራው ሥራ ከእነዚህ ቁጥሮች ውስጥ ምን ትገነዘባለህ?

3. ሮሜ 15፡20-21
ጳውሎስ ወንጌልን ለመስበክ ይፈልግ የነበረው በየት ነበር? ይህስ ምኞት ሊያድርበት የቻለው ለምንድን ነው? እግዚአብሔር ለሕዝቦች ሁሉ ካለው ምኞት ጋርስ ይህ እንዴት ይያያዛል?



1 ይህ ትምህርት ስለእግዚአብሔር ቃል፣ ስለእርሱ ዓለም ዓቀፋዊ ዓላማ እና፣ ናፍቆት በነበራችሁ አመለካከት ላይ ምን ተጽዕኖ አሳደረባችሁ?

2 ከአብርሃም ጋር በተመሳሳይ መንገድ በእግዚአብሔር የተባረካችሁት እንዴት ነው? በምን መንገድ ለምድር ሕዝቦች ሁሉ በረከት ትሆናላችሁ?

## ለተግባራዊ ሕይወት ጠቃሚ ሐሳቦች

1 ከዚህ ትምህርት ውስጥ በእናንተ ላይ ትልቅ ተጽእኖ ያሳደሩ ሶስት ጥቅሶችን በቃላችሁ አጥኑ፡፡

2 በገጽ 59 በጠቃሚ የጽሑፍ ምንጮች ውስጥ፣ በሚሽን የመጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ላይ የቀረቡትን የ 30 ቀናት እና የ7 ቀናት ተግባራቶች በሙሉ አድርጉ፡፡

3 ይህንን የሚሽንን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ለአንድ ቡድን ካልሆነ ግን ለአንድ ሰው ለማካፈል አስቡበት፡፡

### እውነተኛ ታሪክ

በመንፈሳዊ ህይወት ማደግ የጀመርኩት በኮሌጅ ሳለሁ ነበር፡፡ በመጀመሪያው የበጋ ወቅት የደቀመዝሙር ፕሮጀክትና የሚሽን ኮንፈረንስ ተካፈልኩ፡፡ ከፊት ለፊት የነበረ አንድ ሰው “የእግዚአብሔር ቃል የተለያዩ መጻህፍት ስብስብ አይደለም፤ ከዳር እስከ ዳር አንድ የጋራ መሪ ኃሳብ ያለው አንድ ወጥ መጽሐፍ ነው፤ የእግዚአብሔር ክብር በምድር ላይ ወዳሉ ህዝቦች ሁሉ ይወጣል፡ እናንተም የዚህ አካል እንድትሆኑ እግዚአብሔር ይፈልጋል” ብሎ ሲናገር ሰማሁ፡፡ ስለዚህም ከዚያ በኋላ ያሉትን ሁለት ቀጣይ አመታት እግዚአብሔር ለዚህ ዓለም ያለውን ልብ ለማየት በቃሉ ውስጥ ጠልቄ ገባሁ፡፡ እግዚአብሔር በሚሠራውና ሊሠራ ባለው ነገር ውስጥ ዘልዬ መግባት እንዳለብኝ ተገነዘብኩ፡፡ ብዙም ሳይቆይ ወደ ህንድ የምሔድበትና በዚያ ለሒንዱ ከፍተኛ መደብ አባላት ወንጌል ማካፈል የምችልበትን ዕድል አገኘሁ፡፡ ስለዚህም ተነስቼ ሔድኩ፡፡ ዮሐንስ

1 ከተማራችሁት ነገር የተነሳ በዚህ ሳምንት ልታደርጉት የምትፈልጉት አንድ ነገር ምንድን ነው?

2 ስለዚህ ጉዳይ ራሳችሁን ተጠያቂ የምታደርጉለት ሰው ማን ነው?



# ጸልዩ

በየትኛውም እድሜ ላይ ቢገኙ፣ በየትም ቦታ ቢኖሩ፣ ምንም ዓይነት ሥራ ቢሠሩ፣ ጸሎት ለእንዳንዱ የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታይ የተሰጠ ትልቅ እድል ነው፡፡ የሚያሳዝነው ግን ኢየሱስ እንድንጸልይ ባስተማረን መንገድ የሚጸልዩት ጥቂቶች መሆናቸው ነው፡፡ በማቴዎስ 6፡9-10 ኢየሱስ ተከታዮቹን፡ "አባት ሆይ፣ ስምህ የተቀደሰ ይሁን፡፡ መንግስትህ ትምጣ፣ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን፡፡" ብለው እንዲጸልዩ አስተምሯል፡፡ዓለም አቀፍ ጸሐፊና አስተባባሪ የሆነው ስቲቭ ሃውቶርን ስለዚህ ጸሎት ሲናገር

> "ይህ ጸሎት የውዳሴ ዐረፍተ ነገር አይደለም፡፡ በመጀመሪያው ቋንቋ የቀረበው 'አባት . . . ሆይ ስምህን ቀድስ' የሚል ጥያቄ ነው፡፡ ይህንን ሀሳብ በሌላ መንገድ ለመግለጽ፡ "አባት ሆይ ስምህ ከፍ ይበል፣ ተለይቶ ይውጣ፣ ከፍ ከፍ አድርገው፣ ይገለጥ፣ ስምህን ለምድር ሕዝቦች ግለጥላቸው፣ ከማንነትህ የተነሳ ታዋቂ ሁን፣ የምድር ወገኖች ያወቁህና ያደንቁህ ዘንድ አድርግ፡፡" ጸሎቱ በተሟላና ዓለም አቀፋዊ ይዘት ባለው መልኩ "በሰማይ እንደሆነ እንዲሁ በምድር" በሚል ሊጸለይ ይችላል፡፡"

የእግዚአብሔር አንድ ዓላማና ናፍቆት ወደ ፍጻሜ ሲደርስ ለማየት አሁን ባለንበት ሆነን ከእርሱ ጋር አብረን ለመሆን እንደምንችል ማወቅ እንዴት የሚያስደስት ነገር ነው፡፡ በዚህ ክፍል ህልምና ራዕይ ከማየት ውጪ ወንጌል ለመስማት ምንም እድል በሌላቸው ወይም ሰፊ ዕድል በሌላቸው የምድር ሕዝቦች መካከል የእግዚአብሔር ስም የተቀደሰ እንዲሆን እንጸልያለን፡፡

## ማልዱ

1. አባት ሆይ ስምህን ከምድር ሕዝቦች ሁሉ ዘንድ ትቀድስና ታከብረው ዘንድ እንለምንሃለን፡፡ ይኸው ልክ በሰማይ እንደሆነው ሁሉ በምድር ባሉት ህዝቦች ሀሉ ዘንድ መንግሥትህ ትምጣና ፈቃድህም ይፈፀም ዘንድ ነው፡፡

1. የሰማይና የምድር ጌታ ሆይ ለአብርሃም ፣ ለዳዊት፣ ለዳንኤልና ለጳውሎስ ሰዎች ሁሉ ያውቁህ ዘንድ ራእይን እንደ ሰጠሃቸው እኔና ቤተክርስቲያንህን ሁሉ ተመሳሳይ ራእይን በተግባር እንድንኖረው እርዳን፡፡

3. አባት ሆይ መከሩ ብዙ እንደሆነና እንዲሆኑ ተናግረሃል በመሆኑም የመከሩ ጌታ ሠራተኞችን ወደ መከሩ እንድትልክ እንለምንሃለን፡፡



# ትምህርት 2
# የእግዚአብሔር ዓለም፡- ሐሙኅቡሂ

“ለሕዝብ ሁሉ ምስክር እንዲሆን፣ ይህ የመንግስት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል፤ ከዚያም መጨረሻው ይመጣል፡፡” ኢየሱስ

## ዝግጅት

### ዓለም ያለበት ሁኔታ

ባለፈው ትምህርታችን እግዚአብሔር በአብርሃምና በዘሩ (እኛ) በኩል የምድር ሕዝቦችን ሁሉ ለመባረክ የሰጠውን የተስፋ ቃል፣ እንዲሁም የዚህን ተስፋ ፍጻሜ በራዕይ 7፡9-10 ተመልክተናል፡፡ ታዲያ “የዚህን ተስፋ ፍጻሜ ለማየት ምን ያህል ቀርበናል? የሚቀረን ሥራ ምንድን ነው?” የመሳሰሉትን ጥያቄዎች መጠየቃችን አይቀርም፡፡

#### ለሚከተሉት ጥያቄዎች እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልስ ስጡ፡፡

እውነት ወይም ሐሰት
በ100ዓ.ም. የማያምኑ ሰዎች ቁጥር ከአማኞች ጋር የነበረው ጥምርታ 360 ለ1 ነበር፡፡ ዛሬ ግን ከ14 ሰዎች አንዱ ወንጌላዊ ክርስቲያን ነው፡፡

እውነት ወይም ሐሰት
የወንጌላውያን ክርስትና በዓለም ላይ በፍጥነት በማደግ ላይ የሚገኝ ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴ ነው፡፡

እውነት ወይም ሐሰት
የሰሜን አሜሪካና የአውሮፓ ወንጌላውን ክርስቲያኖች በጠቅላላ ሲደመሩ ከሚገኘው ቁጥር ይልቅ የአፍሪካ ወንጌላውያን ክርስቲያኖች ቁጥር ይበልጣል፡፡

እውነት ወይም ሐሰት
በዓለም ዙሪያ ጌዲዮናውያን አንድ ሚሊዮን የቃሉን ቅጂ በየ4.5 ቀን ተኩል ያከፋፍላሉ፡፡

እውነት ወይም ሐሰት
በዓለም ዙሪያ ያሉ ብዙ ሙስሊሞች ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ህልሞችንና ራዕዮችን እየተቀበሉ ነው፡፡

እውነት ወይም ሐሰት
ከጠቅላላው የእስላማዊቷ ኢንዶኔዢያ ሕዝብ የአማኞች ቁጥር ወደ 15 % ተጠግቷል፡፡

እውነት ወይም ሐሰት
ከጠቅላላው የባህል ዘለል አገልጋዮች ውስጥ ከ85% እስከ 95% የሚሆኑት በማገልገል ላይ የሚገኙት በተደረሱ አካባቢዎች ነው፡፡

እውነት ወይም ሐሰት
በዓለም ላይ ከሚገኙት ከ6900 በላይ ቋንቋዎች ውስጥ 30% የሚሆኑት ገና በቋንቋቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ያስፈልጋቸዋል፡፡

እውነት ወይም ሐሰት
በዓለም ላይ ከ2.9 ቢሊዮን በላይ የሚሆኑ ሰዎች ወንጌል ለመስማት ያላቸው ዕድል እጅግ አነስተኛ ነው ፡ ወይም ጭራሹኑ ተደራሽ አይደሉም፡፡

እውነት ወይም ሐሰት
ሲሶው የዓለም ሕዝብ ራሱን ክርስቲያን ብሎ ይጠራል፣ ሌላው ሲሶ ደግሞ ወንጌል በደረሳቸው ሕዝቦች መካከል የሚኖሩ የማያምኑ ሰዎች ሲሆኑ፣ የቀረው ሲሶ ደግሞ ወንጌል ባልደረሳቸው ሕዝቦች መካከል የሚኖሩ ናቸው፡፡

ሂ ፤ሂ ፤ሂ ፤ሂ ፤ሂ ፤ሂ ፤ሂ ፤ሂ ፤ሂ ፤ሂ -፡ሀፃወ

[የሕዝብ ቡድን]
ትልቁ የሕዝብ ቡድን የሚባለው እንደ ቋንቋ፣ ብሔር፣ ሃይማኖት፣ ባህል፣ ታሪክ፣ ወዘተ ያሉ የግንዛቤና የመቀባበል እንቅፋቶች ሳያጋጥመው ወንጌል በቤተክርስቲያን ተከላ እንቅስቃሴ የሚስፋፋበት ሲሆን ነው፡፡

[የተደረሱ ሕዝቦች]
ከሕዝብ ቡድኖች ውስጥ ሕዝቡን በወንጌል ለመድረስና ደቀመዝሙር ለማድረግ የሚችሉ ከ2% በላይ የአገሬው ሕዝብ አባላት የሆኑ ወንጌላውያን አማኞች ያሉባቸው ናቸው፡፡

[ያልተደረሱ ሕዝቦች]
የራሳቸውን ሕዝብ በወንጌል ለመድረስ ከአገሬው ማህበረሰብ የሆኑ በቂ ክርስቲያኖች (ከ2 % ያነሰ የወንጌላውያን ቁጥር) እና ሃብት የሌሉባቸው የሕዝብ ቡድኖች ናቸው፡፡

## ስኬት የሌላቸው የተወሰደ ፤

### 10/40 መስኮት በብርያን ሊ

በኢየሱስ የተሰጠው ትዕዛዝ ሕዝቦችን ሁሉ ደቀ መዝሙር ማድረግ ከሆነ፣ የአስተውሎት ሕግ የሚነግረን ነገር ቢኖር ሥራችን ደቀመዝሙር ያልሆኑትን (የክርስቶስ ተከታይ እንዲሆኑ መማር የሚያስፈልጋቸውን) ሕዝቦች መፈለግ ነው፡፡ ታላቁ ተልዕኮን ለመፈጸም የሚፈልጉ ሰዎች እንዲሁ በሥራ መጠመድ ሳይሆን በሥራቸው ፍሬያማ መሆን እንዲችሉ እነዚህ ያልተደረሱ ሕዝቦች በየት እንደሚኖሩ ማወቅ ያስፈልጋቸዋል፡፡

ከእነዚህ ያልተደረሱ ሕዝቦች መካካል አብዛኞዎቹ የሚኖሩት የ"10/40 መስኮት" የሚል መጠሪያ በተሰጠው የዓለማችን ክፍል ነው፡፡ ይህ 10/40 የሚለው መጠሪያ በላቲቲዩድ የሃሳብ መስመር በ10 ዲግሪ እና በ40 ዲግሪ መካከል ከምዕራብ አፍሪካ እስከ ምስራቅ እስያ የሚገኝ ቦታ ነው፡፡ ይህንን ክልል በካርታ ላይ ለመሳል ከፈለጋችሁ የላይኛ ጣሪያ ከፖርቱጋል እስከ ጃፓን ሲደርስ፣ የታችኛው ወለል ደግሞ ከጊኒ አንስቶ የህንድ ደቡባዊ ክፍል ጫፍ እና እስከ ፊሊፒንስ የሚዘልቅ ይሆናል፡፡ ወንጌልን ለመስማት ዕድል ያላገኙት አብዛኞዎቹ ሰዎች በዚህ አካባቢ ስለሚኖሩ እንደ ክርስቶስ ተከታዮች ስለዚህ ክልል ማሰብ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡


በ10/40 መስኮት ውስጥ የሚኖሩ የጠፉ ሰዎች በጎረቤታችሁ ወይም በቤተሰባችሁ ውስጥ ካሉ ጌታን ከማያውቁ ሰዎች "የበለጠ የጠፉ" አይደሉም፡ ፡ ነገር ግን ወንጌል ለመስማት ዕድሉ የሌላቸው ሆነው የጠፉ ናቸው፡፡

ጉዳዩ እነርሱ ያሉበት የመጥፋት ሁኔታ ሳይሆን፣ ወንጌል ለመስማት ያላቸው ተደራሽነት ነው፡፡




በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ እየኖሩ ወንጌል ያልሰሙ ሰዎች ይኖራሉ፤ ከፈለጉ ግን ለመስማት ይችላሉ፡ ፡ በ10/40 መስኮት ውስጥ የሚኖሩ አብዛኞዎቹ ሰዎች ግን ስለ ኢየሱስ ለመስማት ቢፈልጉም አይችሉም! እነዚህ ሰዎች ወንጌል ለመስማት ተደራሽ ባለመሆናቸው ያልተደረሱ ሰዎች ናቸው፡፡ ዛሬ ከ2.9 ቢሊዩን በላይ የሚሆኑ በወንጌል ያልተደረሱ ሕዝቦች አሉ፡፡ ከእነዚህ ከ2.9 ቢሊዮኑ ውስጥ 97 በመቶ የሚሆኑት በ10/40 መስኮት ክልል ወይም በዚህ ክልል ሲኖሩ ከ1 በመቶ የሚያንሱት ደግሞ በአጠቃላይ በሰሜን እና በደቡብ አሜሪካ ይኖራሉ፡፡

# ጉዳዩ እነርሱ ያሉበት የመጥፋት ሁኔታ ሳይሆን፤ ወንጌል ለመስማት ያላቸው ተደራሽነት ነው ፡፡




በተለያየ ምክንያት ይህ የዓለም ክፍል ሳይደረስ ቀርቷል፡ ፡ በመጀመሪያ እነዚህ ሕዝቦች ምንም መንፈሳዊ እንቅስቃሴ በሌለበት በባዶ ሁኔታ ውስጥ አይኖሩም፡ ፡ የዓለም ታላላቅ ሃይማኖቶች የተጀመሩትና ስር ሰደው የሚገኙት በዚህኛው የዓለማችን ክፍል ነው፡፡ በዚህ 10/40 መስኮት ውስጥ 1.3 ቢሊዮን ሙስሊሞች፣ 860 ሚሊዮን ሂንዱዎች፣ እና 275 ሚሊዮን የቡድሃ ሐይማኖት ተከታዮች ይኖራሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በእዚህ ክልል ውስጥ የሚገኙ አብዛኛዎቹ ሐገራት ወንጌል እንዳይስፋፋ የሚጨቁኑ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ኢየሱስ “መከሩ ብዙ ነው፣ ሠራተኞቹ ግን ጥቂት ናቸው” በማለት ተናግሯል፡፡ ለዚህ የዓለም ክፍል አለመደረስ ትልቁ ምክንያት ወደዚህ ስፍራ ለመሔድ ፈቃደኛ የሆኑ አማኞች አለመኖራቸው ነው፡፡

በአሁኑ ወቅት በተለያየ የአለም ክፍል እየሰሩ ካሉ አጠቃላይ የውጭ ሐገራት ሚሲዮናውያን መካከል ከ10 በመቶ ያነሱት እነዚህን ያልተደረሱ ሕዝቦች ለመድረስ እየሠሩ እንደሆነ ይገመታል፡፡ የቀሩት 90 በመቶ የሚሆኑት ሚሲዮናውያን በወንጌል ባልተለወጡ፣ ነገር ግን በተደረሱ አካባቢዎች ይሠራሉ፡፡ በዓለም አቀፍ ክርስቲያን ኢንሳይክሎፔዲያ መሠረት፡ በዩናይትድ ስቴትስ ለሚሽን ሥራ ከተመደበው ገንዘብ ውስጥ፡ 5.4 በመቶ የሚሆነው ብቻ በውጭ ሐገራት ላሚደረግ የሚሲዮን ስራ ጥቅም ላይ ይውላል፡፡ ከዚህ 5.4 በመቶ ውስጥ ደግሞ 0.37 በመቶ የሚሆነው ብቻ ለወንጌል ተደራሽ ወዳልሆኑ ሕዝቦች ወንጌልን ለማድረስ ስራ ላይ ይውላል፡፡ ይህ ማለት ከእያንዳንዱ አንድ ዶላር ሁለት ሳንቲም ብቻ ለሚሽን ሥራ ይውላል ማለት ነው፡ የተቀረው ገንዘብ ሁሉ በተደረሱ ሕዝቦች መካከል ወንጌልን የበለጠ ለማዳረስ የሚውል ነው፡፡

ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒየር “በዓለም ላይ ከመሃይምነት የበለጠ አደገኛ ነገር የለም” በማለት የተናገረው ነገር የእግዚአብሔርን መንግስት ወደ ፊት ለማራመድ በያዝነው ዓለም አቀፋዊ ስልትም ውስጥ ይህ ትክክል እንደሆነ ያረጋግጥልናል፡፡ ዓለም ያለችበትን ሁኔታ ለማወቅ እና እግዚአብሔር ሕዝቦችን ሁሉ ደቀመዝሙር እንድናደርግ የሰጠንን  ትዕዛዝ ለመፈጸም ያሳየነውን ጥረት በመመዘን ራሳችንን ለማስተማር ጊዜ መውሰድ አለብን፡፡

በዓለም ላይ ላይ ያልተደረሱ ሕዝቦች የሚኖሩበትን ቦታ ለማስታወስ የ10/40 መስኮት ቀላል መንገድ ነው፡ ፡ በእርግጥ ከዚህ አካባቢ ባሻገር በሌላ ስፍራም የሚኖሩ ያልተደረሱ ሕዝቦች አሉ፡፡ ለምሳሌ፦ በዓለም ላይ ትልቁ የሙስሊሞች መኖሪያ የሆነችው ኢንዶኔዥያ የምትገኘው ከ10/40 መስኮት ደቡባዊ ዳርቻ ላይ ሲሆን፣ በመስኮቱ ውስጥ የምትገኘው ደቡብ ኮሪያ ደግሞ እጅግ ብዙ ሚሲዮናዊያንን ከሚልኩ ሐገሮች ተርታ ትመደባለች፡ ፡ የያልተደረሱ ሕዝቦች ጉዳይ የመልክዐ ምድር ሳይሆን የተደራሽነት ጉዳይ ነው፡፡

## ሐሙኀቡሂ ፡- በወንጌል ያልተደረሱ እምነቶች

ከላይ እንዳነበባችሁት በርካታ ያልተደረሱ የዓለም ሕዝቦች የሚኖሩት በ10/40 መስኮት ውስጥ ነው፡፡ ያልተደረሱ ሕዝቦችን ለማስታወስ ቀላሉ መንገድ ሐሙኀቡሂ የሚለውን ምህጻረ ቃል መጠቀም ነው፡፡ (ጸልዩ በሚለው ክፍል ውስጥ እያንዳንዱን ቃል ጠለቅ ብለን እንዳስሳለን፡፡)

| | | |
|---|---|---|
| ሐ | ሐይማኖት የለሽ | 121 ሚሊዮን ሰዎች በ15 ሕዝቦች ውስጥ ይኖራሉ፡ ለእያንዳንዱ 1 ሚሊዮን ሃይማኖት የሌላቸው ሰዎች 12 ሠራተኞች አሉ፡፡ |
| ሙ | ሙስሊም | 1.3 ቢሊዮን ሰዎች በ1344 ሕዝቦች ውስጥ ይኖራሉ፤ ለእያንዳንዱ 1 ሚሊዮን ሙስሊም 6 ሠራተኞች አሉ፡፡ |
| ኀ | የኀሣ ሐይማኖት | 161 ሚሊዮን ሰዎች በ704 ሕዝቦች ውስጥ ይኖራሉ፡፡ ለእያንዳንዱ 1 ሚሊዮን ኀሳዊ ሕዝብ 60 ባህል ዘለል ሠራተኞች አሉ፡፡ |
| ቡ | ቡድሂስቶች | 275 ሚሊዮን ሰዎች በ227 ሕዝቦች ውስጥ ይኖራሉ፤ ለእያንዳንዱ 1 ሚሊዮን ቡድሂስቶች 13 ሠራተኞች አሉ፡፡ |
| ሂ | ሂንዱ | 860 ሚሊዮን ሰዎች በ1843 ሕዝቦች ውስጥ ይኖራሉ፤ ለእያንዳንዱ 1 ሚሊዮን ሂንዱ 2 ሠራተኞች አሉ፡፡ |

1. የቀረበውን ኀዛዊ መረጃ መሠረት በማድረግ ምን አስተያየት ይኖራችኋል?

2. ዮሐ 4፡35 እና ማቴ 9፡37-38 ለእነዚህ የመረጃ አሃዞች ያላችሁ ምላሽ ምንድን ነው? ክርስቶስ ሂዱ፤ ሕዝቦችን ሁሉ ደቀ መዝሙር አድርጉ በማለት ክርስቶስ ከሰጠው ትዕዛዝ አንጻር፡ ወዳልተደረሱት የሚሔዱት ሰዎች ቁጥር አነስተኛ የሆነው ለምን ይመስላችኋል?

3. 2ኛ ተሰሎንቄ 1፡8-10፤ ሮሜ 6፡23፤ ዮሐ 14፡6፡- በኢየሱስ ላይ የማይታመኑ ሰዎች ለዘላለም ከእግዚአብሔር የተለዩ እንደሚሆኑ ታምናላችሁ? ይህ ስለ ኢየሱስ ለመስማት ምንም ዕድል ለሌላቸው ሕዝቦች ምን ማለት ነው? ይህንን ከልባችሁ የምታምኑ ከሆነ ምን ለማድረግ ትነሳላችሁ?

4. ዕንባቆም 2፡14፤ ማቴዎስ 24፡14፡- ያልተደረሱ ሕዝቦችን በሚመለከት ከላይ በቀረበው የቁጥር መረጃ መሠረት እነዚህ ጥቅሶች ምን ተስፋ ይሠጡናል?

# ተግብሩ

1. እነዚህን ነባራዊ እውነታዎች በትምህርት 1 ውስጥ እግዚአብሔር ለሕዝቦች ስላለው ልብ ከተማራችሁት ጋር እንዴት ታነጻጽሩታላችሁ?

2. ይህ ትምህርት የእግዚአብሔርን ዓለም በአዲስ መንገድ እንዴት እንድታዩት አደረጋችሁ?

## ጠቃሚ ኃሳቦች

1. ከjoshuaproject.net እና/ወይም operationworld.org ድረ ገጽ ላይ ተመልከቱና ስላልተደረሱ ሕዝቦች አንዳንድ ነገሮችን ተማሩ፡፡ በተለይም THUMB የሚለውን የጸሎት ቪዲዮ በ joshuaproject/resources/prayer_videos ተመልከቱ ፡፡

2. ስላልተደረሱ ሕዝቦች በቋሚነት መጸለይን የዕለት ውሎ ተግባራችሁ ውስጥ አካቱት፡፡ ምናልባት ከምግብ ሰዓት በፊት፣ ወደ ወደ መኝታ ከመሔድ በፊት ወይም ደግሞ ማለዳ በ 11፡00 ሰዓት ላይ ልታደርጉት ትችላላችሁ፡፡

3. ሐሙጎቡሂን ለሶስት ጓደኞቻችሁ አካፍሏቸው፡፡

## እውነተኛ ታሪክ

የ9 ዓመት ልጅ ሳለሁ እግዚአብሔር የሞንጎሊያን ሕዝብ በልቤ አስቀመጠ፡፡ በትምህርት ቤት የተሰጠኝን የቤት ሥራ ለመሥራት ጥናት ባደረግሁበት ጊዜ በመላው ሐገሪቱ የሚታወቀው የክርስቲያኖች ቁጥር ከ10 በታች እንደሆነ ተረዳሁ፡፡ በየቀኑ የምልጃ ጸሎትን መጸለይ ጀመርኩ፡፡ ስለሕዝቡ የተማርኩትንና ስለእግዚአብሔር የማውቀውን መሠረት በማድረግ ቀላል ጸሎት መጸለይ ቀጠልኩ፡፡ . . .በመኖሪያ ድንኳናቸው ያለው የቡድሂስቶች መሠዊያ በመጽሐፍ ቅዱስ እንዲተካ፣ . . . የኢየሱስን ስም ሰምተው ለማያውቁ ሶስት ሚሊዮን ሞንጎላውያን እግዚአብሔር ወንጌል የሚነግሯቸውን አማኞች እንዲልክላቸው ጸለይኩ፡፡ ለሁለት ዓመት ከጸለይኩ በኋላ የተመለከትኩት ተስፋ ለሞንጎሊያ የሚል ጽሑፍ ቀልቤን ያዘው፡፡ ጽሑፉ 500 ሞንጎላውያን ወደ ጌታ ኢየሱስ ስለመጡበት መንፈሳዊ እንቅስቃሴ የሚናገር ነበር፡፡ ይህ እንግዲህ እግዚአብሔር ጸሎቴን እየመለሰ መሆኑን ለእኔ ያስታወቀበት መንገድ እንደሆነ ተገነዘብኩ፡፡ ---ተስፋ

1. ከተማራችሁት ነገር የተነሳ በዚህ ሳምንት ልታደርጉት የምትፈልጉት አንድ ነገር ምንድን ነው?

2. ተጠያቂ የምትሆኑለት ሰው ማን ነው?


## ሐየ.ሙ.ጎ.ቡ.ሂ፡-ጎሣዊ

በጎሳ ላይ የተመሠረተ እምነት ያላቸው ሕዝቦች በአብዛኛው በፓፑዋ ኒው ጊኒ፣ በአፍሪካና በቻይና ይኖራሉ፡፡

### የጎሣ አባላት እምነቶች

- እነዚህ ሰዎች ተፈጥሮን ያመልካሉ፣ ምትሃታዊ እምነቶችም አሏቸው (ሁሉም ነገር በውስጣቸው መንፈስ አላቸው የሚል አስተሳሰብ፡ ለምሳሌ ውሃ፣ ዐለት ድንጋይ፣ ዛፎች፣እንስሳት)፡፡
- እነዚህን መናፍስት ላለማስቀየም ይጠነቀቃሉ፡፡ መስዋእት በማቅረብ ቁጣቸውን ለማብረድ ይሞክራሉ፡
- አብዛኛውን ጊዜ ጣኦታትን ቅድመ አያቶቻቸውንና የአያቶቻቸውን መንፈስ ያመልካሉ፤ ወደ ጥንቋዮችም ይሔዳሉ፡፡





## በቬትናም ሚኖሩ በቀለማቸው ጥቁር የሆኑ የታይደም ጎሣ

804፣000 ሕዝብ (0.1 % ወንጌላውያን)

የታይ ህዝቦች በሰሜናዊ ቬትናም ቀይና ጥቁር ወንዞች ዳርቻ የሚኖሩ ሲሆን ጥቁር ሕዝቦች የተባሉ የሱቶቻቸው ልብስ ጥቁር በመሆኑ ነው ሕዝቡ ጨዋ አክባሪና እንግዳ ተቀባይ ነው ለሰው አዛኝና ተጨዋች ሲሆን በዓል ለማድረግ ማንናውንም አጋጣ ይጠቀማሉ፡፡ ኢኮኖሚያቸው ርጥብ በሆነ የሩዝ ምርት ላይ የተመሰረተ ነው ለምግብና ለሽያጭ ይጠቀሙበታል፡፡ ወንድም ሆነ ሴት እርሻ ያርሳሉ ፤ ይቆፍራሉ፤ ዓሣ ያተምዳሉ፤ ምግብ ያበስላሉ፤ ልጆች ይፀብቃሉ ቤት ያፀዳሉ፤ ልብስ ያጥባሉ ፡፡ አብዛኛው የታይ ሕዝቦች ጎሳዊ ሃይማኖትን ይከተላሉ። ቴራቫዳ ቡዲዝም ከባሕላዊ ቁስ አምልኮ ጋር የተቆራኘ ሲሆን ሕዝቡ ርዳታ ሲፈልግ ወይም ልመና የሚያቀርበው በርኩሳን መናፍስትና በቁሳቁሶች አማካኝነት ነው ወደ ሞቱ ቅድሞ አያቶቻቸው በመፀለይ አያቶቻቸውን ያመልካሉ እንዲሁም በማንኛው ሰውና ቁስ ውስጥ መናፍስት እንዳሉ ያምናሉ፡፡ በጠባቂ መናፍስትና በአካባቢው መናፍስት ያማናሉ፡፡ እነርሱን ማስቆጣት እንደሌለባቸው ሚያምኑ ሲሆን የመርገምና የበረከት ምክንያት እንደሆኑ ያምናሉ



## ማልዱ

1. በሰማይ በከፍታ ያለህ አምላክ ሆይ የታይ ሕዝቦች መንፈስ ቅዱስን እንዲቀበሉና ከክፉ መናፍስት ነፃ እንድታወጣቸው እንለምንሃለን፡፡

2. አባት ሆይ የታ ሕዝቦች መከር መከርን እንድትባርክ እንጠይቅሃለን፡፡ ምክንያቱም የበረከት ሁሉ ምንጭ የሆንከውን አንተን ይፈልጉ ዘንድ ነው እንዲሁም አንተ የእውነተኛ ርኅራሄ፣ ደስታ እና እንግድነትን መቀበል ምንጭ እንደሆንክ እንዲገነዘቡ እንለምንሃለን፡፡

3. ጌታ ሆይ ካየነው አኀዛዊ መረጃ ወንጌል ያልደረሰባቸው ቦታዊች ያሉ በመሆኑ አዲስ የገንዘብ ምንጭና አዲስ ሚሺነሪዎችን እንድታዘጋጁ እንለምንሃለን፡፡



# ትምህርት 3
# የእግዚአብሔር ሥራ፡- መጸለይ

ቤተክርስቲያን እንድትጸልይ የሚያስተባብር ሰው ዓለምን በወንጌል ለመድረስ በሚከናወነው ታሪክ ውስጥ ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

አንድሪው ሙሬ

## ዝግጅት

### የእግዚአብሔርን ዓለም አቀፋዊ ሚሽን በጸሎት መቀላቀል

እግዚአብሔር አባታችን አስደናቂ የሆነ ስጦታ ሰጥቶናል፤ ይህም የምልጃ ጸሎት ነው፡፡ ጸሎታችሁ ከእግዚአብሔር ዓላማ ጋር አብሮ በመሆን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማስፈጸም እንደሚሠራ ቆም ብላችሁ አስባችሁ ታውቃላችሁ? መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ልብ ስለሚያውቁ፣ ወደ እርሱ ስለሚጸልዩና፣ እግዚአብሔር በሃይልና በሚያስደንቅ ሁኔታ ሲንቀሳቀስ ስለተመለከቱ ሰዎች ታሪክ የተሞላ መጽሐፍ ነው፡፡ በእግዚአብሔር ሚሽን ውስጥ እንቀላቀልና ለየት ባለው የምልጃ ጸሎት ጉዞ አብረን እንደሠት፡፡

የሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች እውነት ወይም ሐሰት መሆናቸውን በማክበብ ግለጹ፡፡ መልሶቻችሁ ትክክል መሆናቸውን ካመሳከራችሁ በኋላ አብረው የሚሔዱትን ጥቅሶች አንብቡ፡፡

እውነት ወይም ሐሰት
እንደ ክርስቲያን በቅድሚያ የምንጋደለው በዚህ ምድር ላይ ከሚኖሩ ሰዎች ጋር ነው፡፡ (ኤፌ 6፡12)፡፡

እውነት ወይም ሐሰት
እንደ ፈቃዱ ስንጠይቀው እግዚአብሔር የሚያስፈልገንን ይሰጠናል፡፡ (1ኛ ዮሐ 5፡14-15)፡፡

እውነት ወይም ሐሰት
እግዚአብሔር ሁሉም ክርስቲያኖች ለሁሉም ሰው እንዲማልዱ ይፈልጋል፤ ምክንያቱም ሰዎች ሁሉ እንዲድኑ ይፈልጋልና ፡፡ (1ኛ ጢሞቲዎስ 2፡1-4)፡፡

እውነት ወይም ሐሰት
መንግስቱን ይሰጣችሁ ዘንድ እግዚአብሔር ደስ ይለዋል፡፡ (ሉቃስ 12፡32)፡፡

እውነት ወይም ሐሰት
ኢየሱስ አንዳንድ ጊዜ ከሕዝቡና ከደቀ መዛሙርቱ ዞር ብሎ ለብቻው ይጸልይ ነበር፡፡ (ሉቃስ 5፡16) ፡፡

እውነት ወይም ሐሰት
በአሁን ሰዓት ኢየሱስ ስለ እኛ ይጸልያል፡፡ (ዕብ 7፡25)፡፡

እውነት ወይም ሐሰት
በሁኔታዎች ላይ በእውነት ለውጥ የሚያመጣ ጸሎት ለተመረጡ መንፈሳዊ ሰዎች ብቻ ነው፡፡ (ያዕቆብ 5፡16-18)፡፡

እውነት ወይም ሐሰት
በሚያስፈልገን ጊዜ የሚረዳንን ምህረትና ጸጋ እንድንቀበል ወደ ጸጋው ዙፋን በድፍረት እንድንመጣ ጥሪ ደርሶናል፡፡ (ዕብ 4፡16)፡፡

እውነት ወይም ሐሰት
ለሚሽን ያለውን እድልና ወቅታዊ ፍላጎት ከተመለከትን፣ ጸሎት ትልቅ ምላሽ ነው፡፡ (ማቴ 9፡37-38፣ ሉቃስ 10፡2)፡፡

ስለ ጸሎት ስታስቡ ወደ አእምሮአችሁ ምን ይመጣል?
ስለ ጸሎት ያላችሁ ተሞክሮስ ምንድን ነው?

መልስ፡ ሐ፡ እ፡ እ፡ እ፡ እ፡ እ፡ ሐ፡ እ፡ እ

[መማለድ]

በሌላ ሰው ቦታ ሆኖ ወደ እግዚአብሔር መጸለይ፣ በሌላው ሰው ትግል ውስጥ ዓላማውን ደግፎ ትግሉን መቀላቀልና ስለዚያ ሰው መሟገትና መለመን ነው፡፡


# ለእግዚአብሔር ፈቃድ መጸለይና ለውጥን ማየት

በታይተስ ኤች

ኢየሱስ ለተከታዮቹ "አሕዛብን ደቀመዝሙር አድርጉ" በማለት ተልዕኮን ደግሞም የማስታረቅ አገልግሎትን ሰጥቷቸዋል፡፡ "በኢየሩሳሌም፣ በይሁዳ፣ በሰማሪያና እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ" ብሏቸዋል (ማቴ 28፡19፣ 2ኛ ቆሮ 5፡18፣ ሐዋ 1፡8)፡፡ ኢየሱስ ሁላችንም በአካል እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ መሔድና ደቀመዝሙር ማድረግ እንደማንችል ያውቃል፡፡ ሆኖም ሁላችንም የየራሳችንን ድርሻ እንድንወጣ ይጠብቅብናል፡ ፡ እያንዳንዱ አማኝ "እስከ ምድር ዳርቻ" ለተባለው ተልዕኮ ከእግዚአብሔር ጋር በቀጥታ በመሠለፍ፡ አስገራሚና ተጨባጭ በሆነ መንገድ ለውጥ ማምጣት እንዲችል ድንቅ ብቃትን ሠጥቶታል፡፡ ይህንንም ብቃት ጸሎት ብለን እንጠራዋለን፡፡

ኢየሱስ ለተከታዮቹ "አሕዛብን ደቀመዝሙር አድርጉ" በማለት ተልዕኮን ደግሞም የማስታረቅ አገልግሎትን ሰጥቷቸዋል፡፡ "በኢየሩሳሌም፣ በይሁዳ፣ በሰማሪያና እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ" ብሏቸዋል (ማቴ 28፡19፣ 2ኛ ቆሮ 5፡18፣ ሐዋ 1፡8)፡፡ ኢየሱስ ሁላችንም በአካል እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ መሔድና ደቀመዝሙር ማድረግ እንደማንችል ያውቃል፡፡ ሆኖም ሁላችንም የየራሳችንን ድርሻ እንድንወጣ ይጠብቅብናል፡ ፡ እያንዳንዱ አማኝ "እስከ ምድር ዳርቻ" ለተባለው ተልዕኮ ከእግዚአብሔር ጋር በቀጥታ በመሠለፍ፡ አስገራሚና ተጨባጭ በሆነ መንገድ ለውጥ ማምጣት እንዲችል ድንቅ ብቃትን ሠጥቶታል፡፡ ይህንንም ብቃት ጸሎት ብለን እንጠራዋለን፡፡ ህይወት ኢየሱስን በሚከተሉ ሰዎች ሁሉ ውስጥ እንዲሆን የሚጠበቅና የተለመደ እንጂ በተለዩ ሰዎች ውስጥ ብቻ የሚገኝ ልዩ ተግባር አድርጎ የሚመለከተው አይመስልም፡፡

ጳውሎስ "መንፈስም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለ ቅዱሳን ይማልዳል" በማለት በሮሜ 8 ይነግረናል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስም በአብ ቀኝ ቆሞ ስለ ልጆቹ ይማልዳል (ሮሜ 8፡26፣ 34፣ ደግሞም ዕብ 7፡25 ተመልከቱ)፡፡ አንዱ የኢየሱስና የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ለአማኞች መማለድ ከሆነ ከእነርሱ ጋር ተባብረን በተለይ ስለሚሲዮናውያንና ያልተደረሱትን ለመድረስ ስለሚደረገው የእግዚአብሔር ሥራ እንጸልይ፡፡ እንደ ኤልያስ እግዚአብሔርን መስማት እና፣ ከኢየሱስና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በመስማማት መጸለይን ከተማርን፡ የእግዚአብሔር መንግስት "በሰማይ እንደሆነች" እንዲሁ ወደ ምድር እንድትመጣ በሚሠራው ሥራ ውስጥ በጣም አስፈላጊ አካል መሆናችን አያጠራጥርም (ማቴ 6፡10)፡፡



# ወደ ሚወደንና ከእኛም ጋር ህብረት ማድረግ ወደሚፈልግ አብ አባታችን እንጸልያለን፡፡

ጸሎት እኛንም ይለውጣል፡፡ የእግዚአብሔርን ልብ የበለጠ በጸሎት በተማርን መጠን፡ አስተሳሰባችንን እና ድርጊታችንን ይለውጠዋል፡፡ እርሱ የሚወዳቸውን ነገሮች መውደድ እንማራለን፤ የሚጠላቸውን ነገሮች እየጠላን እንመጣለን፤ ነገሮችን እርሱ እንደሚያይ እኛም እናያለን፡፡ ለምሳሌ፡- እግዚአብሔር ሐዋርያው ጴጥሮስን በጸሎት አማካኝነት ብዙ ለውጦታል፡፡

በሐዋ 10፡9 "ጴጥሮስ እኩለ ቀን ገደማ ሲሆን፣ ለመጸለይ ወደ ሠገነት ወጣ፡፡" ሲጸልይም ሳለ እግዚአብሔር ጴጥሮስን ተናገረው፤ ጴጥሮስም በቶሎ "እርሱን የሚፈሩትንና ጽድቅን የሚያደርጉትን ሁሉ ከየትኛውም ወገን ቢሆኑ ይቀበላቸዋል" የሚለውን የእግዚአብሔርን መልዕክት ለማስተዋል ችሎ ነበር (ሐዋ 10፡35) ተብሎ ተጽፏል፡፡ ይህ በጴጥሮስ አመለካከት ላይ መሠረታዊ ለውጥ አምጥቷል፤ አልፎ ተርፎም በብዙዎች ላይ በቤተክርስቲያን ውስጥ ትልቅ የአመለካከት ለውጥ መፍጠር ችሏል (ሐዋ 10፡45፣ 11፡18፣ 15፡14-19)፡፡

ያለፉትን ጊዜያት በጨረፍታ ስንመለከት፡ በታሪክ ምዕራፎች ሁሉ ጸሎትና የሚሽን እንቅስቃሴ የተያያዙ መሆናቸውን እናያለን፡፡ አምስት የኮሌጅ ተማሪዎች የከብቶች ምግብ በተከመረበት ስፍራ ላይ ከከባድ ዝናብ ለመጠለል ያደረጉትን የጸሎት ስብሰባ ተከትሎ የአሜሪካን የሚሽን እንቅስቃሴ በ1806 ተወለደ፡፡ በእስያ ስላለው መንፈሳዊ ጨለማ ተወያዩ፣ እያንዳንዱ ክርስቲያን አንድ ነገር የማድረግ ኃላፊነት እንዳለበት ከተነጋገሩ በኋላ መጸለይ ጀመሩ፡፡ ይህ ክስተት እነዚሁ ሰዎች ራሳቸውን ለታላቁ ተልዕኮ አገልግሎት እንዲሰጡ ሲያደርግ፡ "የገለባው ክምር የጸሎት እንቅስቃሴ" ደግሞ ተስፋፍቶ ብዙ አሜሪካውያን ወንጌል ለመስበክ ወደ ባህር ማዶ እንዲላኩ በርካታ የሚሽን ኤጀንሲዎችን በመፍጠር ውጤት አስገኝቷል፡፡

ኢየሱስ "መከሩ ብዙ ነው፤ ሠራተኞቹ ግን ጥቂት ናቸው የመከሩ ጌታ ሠራተኞችን ወደ መከሩ እንዲልክ ጸልዩ" ብሎ በተናገረው ውስጥ በጸሎትና በመሔድ መካከል ቀጥተኛ የሆነ ቁርኝትን መስርቷል (ሉቃስ 10፡2) ፡፡ የዚህን የጸሎትን ሃይል ወይም ያለማቋረጥ የመጸለይን አስፈላጊነት በፍጹም አሳንሰን ማየት የለብንም፡፡ ወዳልተደረሱት የሄዱት ሰዎች ጥቂቶች የሆኑበት ምክንያት ምናልባት ኢየሱስ ስለሠራተኞች ጸልዩ ያለውን ትዕዛዝ ታዘው የጸለዩት ጥቂት በመሆናቸው ነው ብሎ ለመሟገት ይቻል ይሆናል፡፡

በመጨረሻ ወደማን እንደምንጸልይና ስለምን እንደምንጸልይ በደንብ ማስታወስ አለብን፡፡ በምንጸልይበት ጊዜ ይህ ድፍረትንና መተማመንን ይሰጠናል፡፡ የምንጸልየው ወደሚወደንና ከእኛም ጋር ህብረት ማድረግን ወደሚፈልገው ወደ አብ አባታችን ነው፡፡ እግዚአብሔር ማንም ሰው ከእርሱ እንዳይለይ ስለሚፈልግ በገዛ ደሙ ሕዝብን ለራሱ ይዋጅ ዘንድ አንድ ልጁን ላከ (ሮሜ 8፡15፣ 2ኛጴጥሮስ 3፡9፣ ዮሐንስ 3፡16፣ ራዕይ 5፡9-10)! አባታችን የጠፉትን ለመድረስ ይናፍቃል፤ ልጆች ለልጆቻቸው መልካምን ስጦታ መስጠት የሚያውቁ ከሆነ፣ የሰማዩ አባታችን ልጆቹ በጠየቁት ጊዜ ምን ያህል አብልጦ "መልካምን ስጦታ" እና መንፈስ ቅዱስን እንደሚሰጣቸው ተናግሯል (ማቴ 7፡9-11፣ ሉቃስ 11፡11-13)፡፡ "ለምኑ ትቀበላላችሁ፤ ፈልጉ ታገኛላችሁ፤ መዝጊያን አንኳኩ ይከፈትላችኋል" (ሉቃስ 11፡9-10)፡፡ የእግዚአብሔር መንግስት የምትሠራው እንደዚህ ነው፤ ይህ የአብ አባታችን፡ የንጉሳችን መንገድ ነው!

# ተወያዩ

ጳውሎስ የክርስቲያኖች ጸሎት በአገልግሎቱ ውስጥ ያለውን ወቅታዊና ነባራዊ እውነታ ሊለውጥ እንደሚችል ያምናል፡፡ በእያንዳንዱ ምንባብ ውስጥ፣ ጳውሎስ በደጋፊዎቹ ጸሎት ላይ በሙሉ ልቡ የሚደገፈው ምን እንዲያደርግለት ነው? የሚታያችሁን ማንኛውንም ነገር ግለጹ፡፡

1. ሮሜ 15፡30-31

2. 2ኛ ቆሮ 1፡8-11

3. ኤፌሶን 6፡18-20

4. ፊሊጵስዩስ 1፡19

5. ቆላስይስ 4፡3-4

6. 2ኛ ተሰሎንቄ 3፡1-2

ከጳውሎስ ጥያቄዎች አንጻር እነዚህ ነገሮች እናንተና ቤተክርስቲያናችሁ በምትደግፏቸው ሠራተኞች ላይ፣ ምናልባትም ኃላፊነቱ ከሠራተኞቹ ይልቅ በሚጸልዩትና በሚልኩት ሰዎች ትከሻ ላይ ሊያርፍ ይችላል፡፡

# ተግብሩ

1 በዚህ ትምህርት ውስጥ (በዝግጅት፣ በሚነበቡና በውይይት ክፍሎች) ከቀረቡት ጥቅሶች ጎልተው የታዩዋችሁ የትኞቹ ናቸው? ስለ ጸሎት በምታስቡት ላይ ትልቅ ተጽእኖ ያሳደሩባችሁ ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች አሉ?

2 ሁላችንም እንጸልያለን፣ ነገር ግን  እግዚአብሔር በምን በምን ጉዳዮች ላይ እንድንጸልይ እየተናገረን እንደሆነ ለመስማት ምን ያህል ቆም ብለን እናስተውላለን? ይህ አስደሳች ነው ወይስ ተስፋ አስቆራጭ?

## ጠቃሚ ሃሳቦች

1 በጣም አስፈላጊ ስለሆነውና በወንጌል ያልተደረሱትን ስለመድረስ ጉዳይ ጸልዩ፡፡ ይኸውም ብዙ ሠራተኞች ወደ መስክ እንዲሠማሩ፣ ሃብትና አቅርቦት ባልተደረሱት ላይ ትኩረት በሚያደርግ ሥራ ላይ እንዲውል እና መንፈሳዊ ምሽጎች እንዲፈርሱ (ሉቃስ 10፥2፤ ኤፌሶን 6፥10) ነው፡፡

2 ከግሎባል ፕሬየር ዳይጀስት ከጆሽዋ ፕሮጀክት ከጆሽዋ  ፕሮጀክት ከፕሬየር ካሴት ከኦፕሬሽን ወርልድ ወይም ዊንዶአን ዘ ወርልድ አንዱን ወይም ሁሉንም ጠቃሚ መረጃ በመፈለግ ለፀሎት መመሪያ ተጠቀሙባቸው፡፡

3 በወንጌል ያልተደረሱ ሕዝቦችን ፎቶግራፎችና ስለእነርሱ የሚናገሩ አንዳንድ መረጃዎችን ይዛችሁ በዓለም ካርታ ዙሪያተሰባበሰቡ፡፡ በዓለም ካርታ ላይ የሚገኙበትን ቦታ ለዩና ጸልዩ፡፡ በህንድ ፈር ቀዳጅ የሆነው ሚሲዮናዊ ዊሊያም ኬሪ እንዲህ ብሏል “የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ፡ የተከፈተ መጽሐፍ ቅዱስና የተዘረጋ ካርታ ያስፈልገናል፡፡” ኬሪ እንዲህ ብሏል “የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ፡ የተከፈተ መጽሐፍ ቅዱስና የተዘረጋ ካርታ ያስፈልገናል፡፡”

## እውነተኛ ታሪክ

በክርስትና ላይ ጥላቻ ባለው ሐገር ውስጥ ሳገለግል ሳለሁ፣ የሐገሬው ሰው በሆነች በአንዲት ሴት ተቸግሬ ነበር፤ ምክንያቱም ይህች ሴት ስለ ኢየሱስ ለመስማት ልቧን ዘግታ ነበር፡፡ በሐገሬ  ያለው ቤተክርስቲያኔ የፅሁድ አገልግሎት ከመጀመራቸው በፊት እንዲጸልዩልኝ ደብዳቤ በኢንተርኔት ላኩ፡፡ በሚቀጥለው ቀን፡ ከዚህች ሴት ጋር እንደገና ተገናኘተን፤ በተነጋገርንም ጊዜ በውስጧ ታላቅ ለውጥ እንደተካሔደ አስተዋልኩ፡፡ ስለመንፈሳዊ ነገር ለመነጋገር ክፍት መሆን ብቻ ሳይሆን፣ ስለ ኢየሱስ መስማት እንደምትፈልግ ገባኝ፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ትልቅ ለውጥ ሊመጣ የቻለው በቤተክርስቲያኔ ከተደረገው ጸሎት የተነሳ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ቲም

1 በጸሎት ማገልገልን እንዴት ትጀምራላችሁ?

2 ራሳችሁን ለማን ተጠያቂ ታደርጋላችሁ?

# ጸልዩ


## ሐሙኅቡሂ - ሂንዱ

ሂንዱዎች በአብዛኛው በህንድና በኔፓል ይኖራሉ፡፡

### የሂንዱ ተከታዮች እምነት

- በሚሊዮን በሚቆጠሩ አማልክቶች ያምናሉ፡፡
  ከሸክላ፣ ከድንጋይ የተሠሩ ጣኦቶችን ወይም ስዕሎቻቸውን ምግብ፣ አበባና ገንዘብ በመስጠት ያመልካሉ፡፡
- ዳግመኛ መፈጠር ብለው በሚጠሩት የመወለድ- መሞት-ዳግም መወለድ ዑደት ውስጥ የተያዙ እንደሆኑ አድርገው ያምናሉ፡፡





### የህንድ ሂንዱ ብራሂሚዎች

58,346,000 ሕዝብ /0% ወንጌላዊያን

ልጁ ዛሬ ጎልማሳ ሆኖአል! የብራሒሚን መሪ ወደ ጉልምስና እንደተሸጋገረ ምልክት የሚሆን ክር የመሰለ ነገር ሰጥቶታል፡፡ በልጁ ላይ ለየት ያለ ቅዳሴ የመሰለ ነገር በማንሾካሾክ ይናገራል፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ አባት ልጁን እንደ ጎልማሳ አቶ ብሎ ይጠራዋል፡፡ ስለዚህም ልጁ አሁን “ሁለተኛ ተወለደ” ማለት ነው፡፡

የሂንዱ ቅዱስ ትምህርቶች የሚባሉትን የያዙት፣ ብራሂሚኖች እነዚህ ናቸው፡፡

ብራሂሚኖች በሒንዱ ማህበራዊ ደረጃዎች በከፍተኛው ደረጃ ላይ የሚገኙ ናቸው፡፡ ይህም ሁኔታ ኢየሱስን እንደ ጌታ ለመቀበል እንዳይችሉ ተግዳሮት ሆኖባቸዋል፤ ብራሂሚን ከደልቲስ (በሂንዱይዝም የማይነኩ የሚባሉ ናቸው) ጋር የቀረበና የተገናኘ ነው፡፡ ብራሂሚኖች የጌታን ወንጌል ለመቀበል ብዙ ችግሮች አሉባቸው፡፡ ክርስቶስ ከአማኞች ሁሉ ጋር ኅብረት አለው፤ ብራሂሚን ግን የማይነኩ ከሚባሉት ሠዎች ጋር አብሮ መሆንን ይቃወማል፡፡ እግዚአብሔር የዘላለም ሕይወትን ይሰጠናል፤ ብራሂሚን የሚያምነው ግን ለብዙ ጊዜ ደጋግሞ ከመወለዱ በኋላ ፍጹም በረከት ወደ ሞላው የሕይወት ደረጃ ለመግባት መቅረቡን ነው፡፡ በአእምሮው የሚያስበው ክርስቶስን መቀበል ማለት ሁሉንም እንደማጣት አድርጎ ነው፡፡



## ማልዱ

1. ከፍ ብለህ ያለህ እግዚአብሔር ሆይ በቀለማቸው ጥቁር የሆኑ የታይ ሕዝቦችን መንፈስ ቅዱስ ያገኛቸው ዘንድ እና ከክፉ መናፍስት እስራት ሁሉ ነፃ እንዲወጡ እንለምንሃለን፡፡

2. አባት ሆይ የጥቁር ታይ ሕዝቦችን መከር ትባርክ ዘንድ እንለምንሃለን ይኸውም በረከቶችን የምትሰጠውን አንተን ይፈልጉ ዘንድ ነው፡፡

3. ጌታ ሆይ ካነበብነው መረጃና በወንጌል ያልተደረሱ ሕዝቦችን  ዘንድ ካለው የወንጌል ሥራ ተነሣ አዲስ የገንዘብ ምንጭና አዲስ ሚሽነሪዎችን ለእነዚህ ህዝቦች እንድናስነሣ እንለምንሃለን፡፡



# ትምህርት 4
## የእግዚአብሔር ሥራ:- መላክ

ጌታን የማያውቁ ሰዎች ሕይወታችንን በሚሲዮናዊነት በከንቱ የምናሳልፈው ለምን እንደሆነ ይጠይቃሉ፡፡ እነርሱም ሕይወታቸውን እያባከኑ እንዳለ ዘንግተዋል፡፡ የአረፋ የተሞላ የህይወታቸው ኳስ ሲፈነዳ ለዓመታት ያባከኑት ህይወታቸው አንዳችም ዘላለማዊ ዋጋ ያለው ነገር አያሳይም፡፡ ናቴ ሳይንት

## ዝግጅት

### ቡድን “ሀ” እና ቡድን “ለ”

ትምህርት 1 በሰጠን ጥቅሶች እና ትምህርት 2 ባሳየን ሁኔታዎች መሰረት ሁላችንም ወደ 10/40 መስኮት መሔድ ያለብን አይመስላችሁም? በእርግጥ የተወሰኑ ሰዎች መሔድ አለባቸው፤ ሁላችንም ግን ልንሔድ አንችልም፡፡ ሒያጂዎች ወይም ተላኪዎች የሚልካቸው ሰው ያስፈልጋቸዋል፡፡ የጠንካራ ሒያጅን ያህል ጠንካራ ላኪም መሆን አስፈላጊ ነው፡፡

የሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች እውነት ወይም ሐሰት መሆናቸውን በማክበብ ግለጹ፡፡ መልሶቻችሁ ትክክል መሆናቸውን ካመሳከራችሁ በኋላ አብረው የሚሔዱትን ጥቅሶች አንብቡ፡፡

እውነት ወይም ሐሰት
እንደ ላኪ ሆኖ ማገልገል ማለት ገንዘብ መስጠት ማለት ነው፡፡

እውነት ወይም ሐሰት
ጥሩ ሥራ እስከሚኖራችሁ ድረስ ላኪ መሆን አትችሉም፡፡

እውነት ወይም ሐሰት
ላኪ የሆነ ሰው ራሱ ባህል ዘለል ሠራተኛ ሊሆን አይችልም፡፡

እውነት ወይም ሐሰት
እንደ እውነቱ ለሚሲዮናዊያንና ላልተደረሱ ሰዎች ከመጸለይ ይልቅ ገንዘብ መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡

እውነት ወይም ሐሰት
ከገቢያችን አሥር በመቶ ለቤተክርስቲያን ወይም ለሚሽን እስከሰጠን ድረስ የቀረውን ገንዘባችንን እኛ እንደፈለግነው ለመጠቀም ነጻነት አለን፡፡

እውነት ወይም ሐሰት
በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በዚህ ዓይነት መልክ ይኖር የነበረ ሰው ምሳሌ ስላልተሰጠ ሚሲዮናዊያን የገንዘብ ድጋፍ ማሰባሰብ የለባቸውም፡፡

እውነት ወይም ሐሰት
በባሕር ማዶ ለማገልገል የተሰማሩት በእኛ ላይ ሳይሆን በእግዚአብሔር ላይ ይደገፉ ዘንድ ተግባራዊ በሆነ መንገድ መንከባከብ ለምሳሌ:- አንዳንድ ጠቃሚ የሆኑ ቁሳቁሶችን መላክ ጥሩ አይደለም፡፡

እውነት ወይም ሐሰት
ለሚሽን ሥራ ከሚሰጠው ከእያንዳንዱ ዶላር ወዳልተደረሱት ወንጌልን ለመውሰድ የሚውለው ከ2 ሳንቲም የሚያንሰው ብቻ ነው፡፡

**ስለ ላኪ ስታስቡ ወደ አእምሮአችሁ የሚመጣው ምንድን ነው?**

ቲሩወሂ ፡ቲሩወሂ ፡ቲህሦ ፡ቲሩወሂ ፡ቲሩወሂ ፡ቲሩወሂ ፡ቲሩወሂ ፡ቲሩወሂ ፡ቲህሦ ፡ህፃመ

### [ላኪ]

ላኪ ማለት ለተወሰኑ የባህል ዘለል ተላኪዎች ስራ እና በአጠቃላይ ዓለም አቀፉን የወንጌል ሥራ ለመደገፍ ሃብቱን በፈቃደኝነት የሚያውል ማለት ነው፡፡

# አንብቡ

## መላክ

### በአንድ የተጓዥ ቡድን ጽሑፍ ላይ ተመስርቶ የቀረበ

ሐዋርያው ጳውሎስ “ካልተላኩስ እንዴት ይሰብካሉ?” ብሎ ሲናገር የሚያስገርምና ቀልብ የሚስብ ምልከታ እንደ ነበረው ያሳያል (ሮሜ 10፡15)። የሚሔዱትን በዚያው በአገራቸው ያሉ ሰዎች በገንዘብ ካልደገፉና ካልጸለዩላቸው ያልተደረሱት ወንጌል መስማት የሚችሉበት ዕድል የለም። ይህ ማለት፣ የበለጠ አስፈላጊው የትኛው ነው? “ሕይወት ለማዳን ወደ ጉድጓድ ውስጥ የሚወርደው ወይስ፣ በጉድጓዱ አናት ላይ ሆኖ የገመዱን ጫፍ የሚይዘው ሰው?” ብሎ እንደመጠየቅ ነው። አንዱ ያለ ሌላው ሊኖር አይችልም።

በእኛ በአሜሪካኖች ባህል ገቢያችን የትኛውንም ያህል ይሁን እንደ ገቢያችን መጠን እንኖራለን ተብሎ ይታሰባል። የአንድ ሰው ገቢ በጨመረ መጠን የኑሮ ደረጃውም እንደዚያው ይጨምራል። ነገር ግን ዓለም አቀፍ ክርስቲያኖች ከዚህ የተለየ አስተሳሰብ ሊኖራቸው ይገባል። ክርስቲያን ገቢው ሲጨምር ወይም ያልተጠበቀ ገንዘብ ሲያገኝ፣ እግዚአብሔር ያንን ሰው ለሌላው ሰው የሃብት ምንጭ እንዲሆን ይፈልገዋል። እንዲህ ዓይነቱ አስተሳሰብ ከባህሉ ጋር የሚጣረስ እንደሆነ ይታወቃል።



# ካልተላኩ እንዴት ይሰብካሉ?

በወጣትነት ዕድሜ ላይ የሚገኙ የማውቃቸው ጥንዶች፡ በቅርቡ ፍጹም የአመለካከት ለውጥ አምጥተው የላኪነት ድርሻቸውን ለመወጣት ኃላፊነት ወስደዋል፡፡ እነዚህ ጥንዶች የግል በጀትን በተመለከተ ራስን ማስቀደም ሳይሆን መስጠትን ቅድሚያ በማድረግ እንደ ባህላችን ለራሳችን የግል ጥቅም የምናውለውን የገንዘብ መጠን ስለማስተካከል የተፃፈ ፅሁፍ አነበቡ፡፡ ቀድሞውኑም ቢሆን ሚሲዮናውያንን በመስጠት ይደግፉ ነበር፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ለሕዝቦች ሁሉ ካለው አላማ አንጻር ይህንን የበለጠ ቅድሚያ መስጠት እንዳለባቸው ተረዱ፡፡ የሚያሳዝነው ግን በሚቀጥለው ዓመት በአካባቢው ከነበረው ወቅታዊ ችግር የተነሳ ገቢያቸው በግማሽ ቀነሰ፡፡ ይሁን እንጂ በመላክ ላይ ከተመሰረተው ከአዲሱ ትኩረታቸው የተነሳ፡ ከዓመት በፊት ይሰጡት ከነበረው የገንዘብ መጠን ጨምረው ለመስጠት ቻሉ፡፡

ገንዘብ የመስጠትን ልማድ ማዳበር ለብዙ ሰው አስቸጋሪ ነው፤ ምክንያቱም ሁል ጊዜ የሚሰማቸው ስሜት ገንዘብ እንደሌላቸው (ገንዘብ እንደሚያንሳቸው) ነው፡፡ ነገር ግን ዋናው ጉዳይ የምንሰጠው የገንዘብ መጠን ሳይሆን፡ ያለህን ሃብት ሁሉ ገንዘብን ጨምሮ ከእግዚአብሔር መንግስት አንጻር ተገቢውን ቅደም ተከተል እንዲይዝ ማድረግ ነው፡፡

በግልጽ የሚታወቀው ትልቁ የመላክ ገጽታ ሚሲዮናዊንን ለመደገፍ ገንዘብን መስጠት ነው፡፡ ነገር ግን በእርግጠኝነት የመላክ ገጽታ ይህ ብቻ አይደለም፡፡ ላኪ የሆነ ሰው ከሚከተሉት ልዩ ልዩ ሚናዎች አንዱን ወይም ሁሉንም መጫወት ይችላል፡፡ እነዚህም፡- የቁሳቁስ አቅርቦት፣ ጸሎት ማስተባበር፣ መረጃን የማስተላለፍ ተግባር፣ ጥናትና ምርምር፣ ፋይናንስ ወይም እንደገና የሚሠማሩትን ማስተባበር የመሳሰሉት ናቸው፡፡ የቁሳቁስ አቅርቦት ሚናን የሚጫወተው ሰው፡ ለሚሲዮናዊ የሚሆኑ ዕቃዎችን በማሸግ፣ የበረራ ወይም የጉዞ ዕቅድ በማመቻቸት፣ በመስክ ላይ የሚፈለጉ ነገሮችን በማሰባሰብ የመላክን ተግባራዊ ሥራዎች ሊሠራ ይችላል፡፡ የጸሎት አስተባባሪ፡ በመስክ ላይ ካሉ ሚሲዮናዊያንና ከሚሽን ኤጀንሲዎች በተገኘ ጥናት ላይ በመደገፍ ለጸሎት የሚያስፈልጉ ጉዳዮችን ይለያል፡፡ በተጨማሪም ለቡድኑ የምልጃ ጸሎት እንዲያደርጉ ሌሎችን ለማነሳሳትና ልዩ የጸሎት ስብሰባዎችን በማደራጀት ማገልገል ይችላል፡፡ ሌሎች ሰዎች የጸሎት ርዕሶችን እና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን እንዲያውቁ፡ የመረጃ አስተላላፊዎች ትልቅ እገዛ ያደርጋሉ፡፡ በመስክ ላይ ባሉትና በጸሎት ቡድኑ መካከል የግንኙነት መስመር እንዲዘረጋና የጸሎት ጥያቄዎችና ሌሎች ጉዳዮች ግልጽ እንዲሆኑ ማድረግ የእነርሱ ኃላፊነት ነው፡፡ የመላክ ሚና በጣም የሚስብም ሆነ ቀላል አይደለም፡፡ ከሚሽን ሥራ ጀርባ ሆኖ የዕለት ተዕለት ኃላፊነትን መወጣት ብዙ ምስጋናን የማያስገኝ ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን ያለብድራት የሚቀር አይደለም፡፡

እንደ ገበሬ ሚስትነቷ፡ አያቴ ሶስት ትናንሽ ልጆቿን እያሳደገች፡ ወደ ባሕር ማዶ ለተሰማሩና ቤተክርስቲያኗ ለምትደግፋቸው ስድስት ሚሲዮናውን፡ በየሳምንቱ በእጆቿዋ ደብዳቤ ትጽፍላቸው ነበር፡፡ ነገሮችን ቀላል ያደረገው የኢሜይል መረጃ መለዋወጫ ከመምጣቱ ብዙ ቀደም ብሎ ሌሎችን መንከባከብና በሩቅ ስፍራ ሆነው ለሚያገለግሉት በረከት መሆን ምን ያህል ታላቅ ዋጋ እንዳለው አይታለች፡፡ እነዚህ ደብዳቤዎች ለሚሲዮናዊያኑ ከሐገራቸው ጋር የሚያገናኙዋቸው አስተማማኝ የግንኙነት ምንጭና ታላቅ ማበረታቻ ነበሩ፡፡ ለዕረፍት ወደ ሐገራቸው በሚመለሱ ጊዜም ከእርሷ ጋር ለቀናት ከመቆየታቸው ባሻገር ታላቅ አክብሮትን ይሰጧት ነበር፡፡ አያቴ የተረዳችው ነገር መላክ ማለት በገንዘብ መደገፍ ብቻ ሳይሆን፣ ተግባራዊ እንክብካቤ መስጠትና በቋሚነት ማበረታታትም ነው፡፡

ወንጌል ለሕዝቦች ሁሉ ይሰበክ ዘንድ የላኪ ድርሻ እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ ብዙ ክርስቲያኖች ይህንን ሚና እየተቀበሉ በመጡ ቁጥር ያልተደረሱትን ለመድረስ የሚደረገው የሚሽን አገልግሎት እንዲያድግና ውጤታማ እንዲሆን ያደርጋሉ፡፡

# ተወያዩ

1. ሮሜ 10፡14-15
ወንጌልን ለሌሎች የማድረስ ተግባር የሚያካትታቸው የተለያዩ ሚናዎች ምንድን ናቸው?

2. ሉቃስ 8፡1-3፣ ማቴዎስ 9፡37-38፣ ሮሜ 15፡30፡-
ኢየሱስን በአገልግሎቱ እንዴት ይደግፉት ነበር? ሰዎች ተሳታፊ እንዲሆኑ የተጠየቁባቸው አንዳንድ መንገዶች ምንድን ናቸው?

3. መዝሙር 24፡1 እና 1ኛ ዜና 29፡14
ንብረታችን የተገኘው ከየት ነው? በባለቤትነትና በባለአደራነት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

4. 3ኛ ዮሐ 5-8 በቁጥር 6
“ለእግዚአብሔር እንደሚገባ” አድርጎ መላክ ማለት ምን ማለት ነው? በቁጥር 8 የመጨረሻ ክፍል ላይ ዮሐንስ በላኪና በተላኪ መካከል ስለሚኖረው ግንኙነት ምን ይላል?

5. ፊሊጵስዩስ 4፡15-19
እንደ ላኪ ስናገለግል፡ ጳውሎስ ምን ዓይነት ነገሮች ይሆናሉ ይላል?

6. 2ኛ ቆሮ 9፡6-12
ጳውሎስ በዚህ ስፍራ በሚያስተላልፈው ትምህርት ውስጥ አንዳንድ የመስጠት መርሖዎች ምንድን ናቸው? እንዴት እንስጥ? ለምን?

# ተግብሩ

1. ገንዘብ ከመስጠት በተጨማሪ የባህል ዘለል ሚሽንን ልትደግፉ የምትችሉበትን ከ3 እስከ 10 የሚደርሱ መንገዶችን ዘርዝሩ፡፡

2. ላኪ በመሆን ውስጥ እናንተም ሆናችሁ በዙሪያችሁ ያሉ ሌሎች ወገኖች የሚያጋጥሟችሁ እንቅፋቶች ምንድን ናቸው?

## ለተግባራዊ ሕይወት ጠቃሚ ሐሳቦች

1. በየወሩ የተጨማሪ ወጪዎቻችሁን (ለምሳሌ፣ ውጪ መብላት፣ መዝናናት) የሚያህል ገንዘብ በቤተክርስቲያናችሁ ለባህል ዘለል አገልግሎት ተልከው ለሔዱ ሰዎች ስጡ፡፡
2. የባህል ዘለል አገልግሎት ተላኪዎችን ዝርዝር ውሰዱና በየዕለቱ ስለእነርሱ መጸለይ ጀምሩ፡፡
3. ባህር ማዶ ላሉ አገልጋዮች ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ የሚያበረታታ ኢሜይል ጻፉ፡፡

## እውነተኛ ታሪክ

ለሒንዱ የኮሌጅ ተማሪዎች ወንጌል ለማካፈል ለአንድ ዓመት ወደ ሕንድ የሔደውን ወዳጄን መደገፍ ጀመርኩ፡፡ በመስጠት አማካኝነት ስለሚጠፉት ሰዎች በልቤ ሸክም አደረብኝ፤ ሕዝቦች በወንጌል ሲደረሱ የማየት ጠንካራ ፍላጎት በውስጤ እያደገ መጣ፡፡ ወዳጄን በመደገፍ ሕዝቦችን ለመባረክ ከመቻሌም በተጨማሪ በሕንድ ሐገር ባለው አገልግሎት ተካፋይ አደረገኝ፡፡ አንዳንድ ጊዜ  ያንን ገንዘብ ለራሴ ጉዳይ ለማዋል ስለምፈልግ ነገሩ ከባድ ነው፡፡ ነገር ግን በቃል ኪዳኔ ጸናሁ፤ በሕይወቴ የእግዚአብሔርን መንግስት ቀዳሚ ለማድረግ በሚያስችል መልኩ ገንዘቤን ሳወጣ ደስ የሚያሰኝ ስሜት ፈጠረብኝ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ መዝገብህ ባለበት ልብህ በዚያ አለ ይላል (ማቴ 6፡21)፡፡ ገንዘቤን ከራሴ በሚያልፍና ለዘላለም በሚቆይ ነገር ላይ ማዋል ፈለግሁ!

ሰለስቴ  የሚባል ሰው የተናገረው

1. እንደ ላኪ በምን ዓይነት መንገድ ማገልገል ትጀምራለህ

2. ራስህን ለማን ተጠያቂ ታደርጋለህ?

# ጸልዩ

## ሃይማኖት አልባዎች


ሐየ.ሙ.ጎ.ቡ.ሂ፡- ሃይማኖት አልባዎች

ሃይማኖት የሌላቸው ሰዎች በአብዛኛው በቻይና፣ በሰሜን ኮሪያ፣ በሰሜን እስያ እና በአውሮፓ ይኖራሉ፡፡

### እምነቶቻቸው

- አንዳንድ የጥንት አባቶቻቸውን መንፈስ የሚያመልኩ፣ ወይም የቡድሐ እምነትን የሚከተሉ ቢኖሩም፡ አብዛኛዎቹ ግን በእግዚአብሔር አያምኑም፡፡ ብዙዎቹ እግዚአብሔር የለም ብለው የሚያስተምሩ ኮሚኒስት መንግስቶች አሏቸው፡፡ አብላጫዎቹ የሚኖሩት ግን በቻይና ነው፡፡





## በቻይና የሚኖሩት የሚንግ ሕዝብ

15,100 ሕዝብ /0 % ወንጌላውያን

ማአክስያን በተባለው የቻይና ግዛት የቡድሒስት ቤተ መቅደሶች እንኳን ባዶ ሆነዋል፡፡ አንድ ትውልድ እንዳለ የክህደት ትምህርት እንዲቀበል ተደርጓል፤ ስለዚህም አሁን የሚንግ ሰዎች ማንኛውንም ዓይነት ሃይማኖታዊ እምነት ሲሰሙ ይሳለቃሉ፡፡ ይህ ወጣቱ ትውልድ ተፈጥሮን የሚያመልኩትን ወይም ቡድሒስት ወላጆቹን "አጉል እምነት ተከታዮች" በማለት ያፌዙባቸዋል፡፡

የወንጌል ጽሑፍ ለማከፋፈል የሚሞክሩ ክርስቲያን ቡድኖች እስራት ይገጥማቸዋል፡፡ በዚህኛው የዓለም ክፍል የሚኖሩ ከ15,000 የሚበልጡ የሚንግ ሕዝብ በክርስቶስ ስለሚገኘው ድነት ይሰሙ ይሆን?

ከዓመታት በፊት እነዚህ ከተደባለቀ ዘር የተገኙት ሰዎች ንቀት ደርሶባቸዋል፡፡ በሃን ቻይናዎች ዘንድ ለማህበራዊ ግንኙነት ተቀባይነት ባለማግኘታቸው፡ የሚንግ ሕዝብ የተለየ ልብስ በመልበስና የራሳቸውን መንደር በመመስረት ራሳቸውን ለይተው ማንነታቸውን ገነቡ፡፡



## ጠቃሚ ሃሳቦች

1. አባት ሆይ ማዕድን ማውጣት ጭቆናና አድልዎች እንዳለበት ታውቃለህ፡፡ ነገር ግን በክርስቶስ እንደተወደዱ ዋጋ እንዳላቸውና ተቀባይነትን እንዳገኙ ግለጥላቸው በአንተ ቤተሰብ ውስጥ ያላቸውን ቦታ አሳያቸው፡፡

2. የፍቅር አምላክ እግዚአብሔር ልባቸው በቁጣ ለተሞላው ማዕድን ሠራተኞች ልብ ውስጥ ፍቅርን ግለጥላቸው፡፡

3. አባት ሆይ በአለም ዙሪያ ያሉ ሰዎችን ጊዜአቸውንና ሀብታቸውን ከታላቁ ተልዕኮ አኳያ እንዲመዝኑ ዕርዳቸው ተጨማሪ ሠራተኞችን መላክ እንድንችል በደስታና በተከፈተ ልብ ምላሽ እንድንሠጥ እርዳን



# ትምህርት 5
## የእግዚአብሔር ሥራ፡- መቀበል

*ያለኝ ሁሉ ሙጥጥ ብለ እኪያልቅ ድረስ ራሴን ለእግዚአብሔር ለመስጠት ዝግጁ ነኝ፣ በሆነ መንገድ አንዳንዶችን የማድን ከሆነ በማንኛውንም ችግር ውስጥ ለመጽናት ተዘጋጅቻለሁ፡፡ የልቤ ናፍቆት ስለ እርሱ ሰምተው በማያውቁት ሰዎች ዘንድ የከበረው አዳኜ የታወቀ እንዲሆን ነው፡፡ ዊሊያም በርንስ*

# ዝግጅት

## በጓሮአችን

እግዚአብሔር ለወንጌል ተደራሽ ካልሆኑ ሕዝቦች መካከል የኮሌጅ ተማሪዎችን፣ ባለሙያዎችን፣ እንዲሁም ቤተሰብን ወደ ሰሜን አሜሪካ እያመጣ ነው፡፡ እነዚህ ዓለም አቀፍ ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ በሐገራቸው ብሩህ አእምሮ ያላቸውና የተመረጡ ሲሆኑ፣ ከእነዚህም ብዙዎቹ በትምህርት ቤት የመኻታ ክፍሎቻችንና ጎረቤቶቻችን ሆነው ይኖራሉ፡፡ በዚህ ትምህርት ከገዛ አገራቸው ርቀው ስላሉ እግዚአብሔር ምን እንደሚያስብና የእርሱን ፍቅር ተጨባጭ በሆነ መንገድ እንዴት ወደ እነርሱ ማድረስ እንደምንችል እንመለከታለን፡፡

የሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች እውነት ወይም ሐሰት መሆናቸውን በማክበብ ግለጹ፡፡ መልሶቻችሁ ትክክል መሆናቸውን ካመሳከራችሁ በኋላ አብረው የሚሔዱትን ጥቅሶች አንብቡ፡፡

**እውነት ወይም ሐሰት**
ዓለም አቀፍ ሰዎችን መቀበል እንግዶችን የመቀበል ስጦታ ያላቸው ሰዎች ኃላፊነት ነው፡፡

**እውነት ወይም ሐሰት**
በየዓመቱ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ የሚኖሩና የሚማሩ ወደ 820,000 የሚጠጉ ዓለም አቀፍ ተማሪዎች አሉ፡፡

**እውነት ወይም ሐሰት**
ብዙ ዓለም አቀፍ ሰዎች አሜሪካኖች ክርስቲያኖች ናቸው ብለው ያምናሉ፡፡

**እውነት ወይም ሐሰት**
በርካታ ዓለም አቀፍ ሰዎች ከአሜሪካኖች ጋር ወዳጅ ለመሆን ጊዜ የላቸውም፡፡

**እውነት ወይም ሐሰት**
ከዓለም አቀፍ ሰዎች ውስጥ የሚበዙት በአሜሪካኖቹ ቤት ፈጽሞ አይጋበዙም፡፡

**እውነት ወይም ሐሰት**
ከዓለም አቀፍ ተማሪዎች ውስጥ ስድሳ በመቶ የሚሆኑት የሚመጡት ከ10/40 መስኮት አካባቢ ነው፡፡

**እውነት ወይም ሐሰት**
በርካታ የዓለም አቀፍ ሰዎች ወደ ሐገራቸው በመመለስ በቢዝነስ፣ በትምህርትና በፖለቲካ መሪዎች ይሆናሉ፡፡

**እውነት ወይም ሐሰት**
ዓለም አቀፍ ሰዎችን በውጤታማ መልኩ ለመቀበል ብዙ ጊዜ፣ ገንዘብ፣ የማጫወት ችሎታና የተዘጋጁ የውይይት ርዕሶች ሊኖሩህ ይገባል፡፡

**ዓለም አቀፍ ሰዎች ሲባል ወደ አእምሮህ የሚመጣው ምንድን ነው? ከሌሎች ሐገራት የመጡ ተማሪዎችንና ቤተሰቦችን በመድረስ በኩል በጣም አስፈሪ ሆኖ የሚሰማህ ምንድን ነው?**

መልሶች፡- ሐ፡ እ፡ እ፡ ሐ፡ እ፡ እ፡ እ፡ ሐ

**[ተቀባይ]**
ዓለም አቀፍ ሰዎችን በእንግድነት ለመቀበል፣ ለማገልገል፣ ወዘተ ጊዜ የሚወስድና እንግድነት እንዳይሰማቸው የሚያደርግ ሰው ነው፡፡

**[ዓለም አቀፍ ሰዎች]**
ከሐገራቸው ወጥተው በሌላ ሐገር የሚኖሩ ተማሪዎች፣ ባለሙያ ሰዎች፣ ስደተኞችና ቤተሰቦች ናቸው፡፡

አንብቡ

# በመካከላችን ያሉ ሕዝቦች

በማይክ ኬ

ወላጆቻችንና አያቶቻችን ከኖሩበት እጅግ በተለየ ዓለም እንኖራለን፡፡ ዓለም እንደ አንድ መንደር በመዋሐድ ሒደት ላይ ስለሆነች፡ በዓለም ዙሪያ ያሉ ሰዎች በየጊዜው ተንቀሳቃሽና እርስ በእርስ የተሳሰሩ እንዲሆኑ በማድረግ አዲስ ዘመንን አምጥቷል፡፡ እንደ ቤተክርስቲያን፡ ኢየሱስ ሕዝቦችን ደቀመዝሙር አድርጉ ብሎ የተናገረውን ትዕዛዝ ለመወጣት ስንሞክር እንዲህ ዓይነቱን ለውጥ ችላ ማለት አንችልም፡፡ አሁን ካለው ዓለም አቀፋዊ አካሔድ አንጻር ስንመለከተው፡ ሕዝቦችን ለመድረስ የበለጠ ውጤታማ እየሆነ የመጣው መንገድ ዓለም አቀፍ ሰዎችን መቀበል፣ እነርሱን ወዳጅ ማድረግና የክርስቶስን ፍቅር ለማሳየት በእንግድነት መቀበል ነው፡፡

ባለፉት ዘመናት፡ ተማሪዎች ሐገራቸውን ትተው ወደ ባህር ማዶ ለጥናት የሚሔዱበት እድል አነስተኛ ነበር፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ዕድል የነበራቸው ሃብታም ሰዎች ብቻ ነበሩ፡፡ አሁን ግን ነገሩ እንደዚያ አይደለም፡፡ ተማሪዎች በተለያዩ መስኮች የትምህርትና የሙያ እድሎችን ፍለጋ ውቅያኖሶችን ያቋርጣሉ፡፡ በዩናይትድ ስቴትስ ብቻ ከ፤ ሚሊዮን የሚበልጡ ዓለም አቀፍ ተማሪዎች ይማራሉ፡፡ ይህ ነገር በምዕራቡ ዓለም ብቻ ያለ ክስተት አይደለም፡፡ በሩሲያ በነበርኩበት ወቅት ከቻይና፣ ከቱርክና ከዓለም



# ዓለም አቀፍ ሰዎችን መድረስ እግዚአብሔር ዓለምን ለመድረስ ላለው ዕቅድ ትልቅ አስተዋጽኦ አለው፡፡

ቀፍ ተማሪዎች ወደ ኒውዮርክም ይሁን፣ ቤይጂንግ ወይም ደግሞ ናይሮቢ ቢሔዱ በውጭ ሐገር ከስድስት ወራት እስከ ስድስት ዓመታት ለሚሆን ጊዜ በትምህርት ላይ ይቆያሉ፡፡ ከዚህ በኋላ ብዙዎቹ በሙያቸው ለመሥራት ወደ ሐገራቸው ይመለሳሉ፡፡ በእነዚህ ኮሌጅ በሚቆዩባቸው ዓመታት ወደ ጌታ ኢየሱስ ቢመጡና ደቀመዝሙር እንዲሆኑ ቢደረጉ ወደ ሐገራቸው ወደ ቻይና፣ ሕንድ ወይም መካከለኛው ምስራቅ ሲመለሱ ትምህርት ይዘው ብቻ ሳይሆን፣ የክርስቶስ አምባሳደር ሆነውም ይመለሳሉ፡፡

ይህንን ስልት "ተመላሽ ሚሽን" ብለን እንጠራዋለን፡፡ ዓለም አቀፍ ሰዎች የሀገራቸውን ቋንቋውና ባህል የሚያውቁ ናቸው፡፡ ወደ ሐገራቸው ሲመለሱና ኑሮአቸውን ሲመሠርቱ የማህበራዊና የዝምድና ግንኙነታቸውን እንደገና ይዘረጋሉ። በሐገራቸው ተጽዕኖ ማሳደር የሚችሉበት አድማስ ይጠብቃቸዋል፡፡ እነዚህ ተማሪዎች የራሳቸውን ሕዝብ እንዲደርሱ በማስታጠቅ ሕዝቦችን ለመድረስ እንችላለን፡፡

የሚያሳዝነው ግን ስታቲስቲክስ የሚያሳየው አብዛኛዎቹ ዓለም አቀፍ ተማሪዎች በውጭ ሐገራት በሚኖራቸው የቆይታ ጊዜ ከባህሉ በመገለል ጊዜያቸውን ለብቻቸው ማሳለፋቸው ነው፡፡ ወደ ቤታችን ለመጋበዝ ዕድል የሚያገኙት ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ አንድ የዳሰሳ ጥናት እንደሚያሳየው በዩናይትድ ስቴትስ ከሚኖሩ ዓለም አቀፍ ተማሪዎች ውስጥ 80 ከመቶ የሚሆኑት የአሜሪካውያን ቤቶች ምን እንደሚመስሉ ለማየት የሚመኙም ቢሆን ዕድል ግን አያገኙም፡፡ የውጭ ሐገር ተማሪዎች በሚማሩባቸው ሌሎች ከተሞችም ቢሆን ይህ ሁኔታ ተመሳሳይ እንደሚሆን አስባለው፡፡ ይህ እንግዲህ ዛሬ ቤተክርስቲያን ሳትጠቀምበት የምታሳልፈው ዕድል ነው፡፡

መጀመሪያው ላይ እንዲህ ባይመስልም ዓለም አቀፍ ተማሪዎች እንደኛው ናቸው፡፡ ቤታቸውንና ቤተሰባቸውን ማጣት ያንገላታቸዋል፡፡ በብቸኝነት፣ በባህል መደናገር፣ አንዳንድ ጊዜም በመደበትም ውስጥ እንኳ ያልፋሉ፡፡ አማኞች በራሳቸው ተነሳስተው ከእነዚህ ተማሪዎች ጋር ግንኙነት ቢጀምሩ ትልቅ ልዩነት ይፈጥራሉ፡፡ የእነዚህ ተማሪዎች አንዱና ትልቁ ፍላጎት ወዳጅነትና በባዕድ ባህል ውስጥ እንዴት መኖር እንዳለባቸው በማሳየት የሚረዳቸውን ሰው ማግኘት ነው፡፡

ተቀባይ መሆን ማለት ምንም የተወሳሰበ ነገር የለውም። ጓደኝነት በመፍጠር ይጀምራል፡፡ በዓለም ዙሪያ ካሉ ዩኒቨርሲቲዎች በገዛ ሕዝባቸው መካከል የክርስቶስ አምባሳደር ሆነው ለመመለስ የሚጎርፉ ሰዎችን አስቡ፡፡ ይህ ለመሆን የሚችለው ቤተክርስቲያን እጇን ዘርግታ መቀበል ስትጀምር ነው፡፡

ሕዝቦች ያሉት እዚህ ነው፡፡ በዓለም ላይ የክርስቶስን ተጽዕኖ ለመፍጠር ዕድሉ በደጃችን ላይ ይገኛል፡፡ እጃችንን ዘርግተን በቤታችንና በቤተክርስቲያናችን በመቀበል ዕድሉን እንጠቀምበት፡፡

# ተወያዩ



1. ዘሌዋዊያን 19፡34፣ ዘዳግም 10፡18-20፡
እነዚህ ምንባቦች እግዚአብሔር ለዓለም አቀፍ ሰዎች ያለውን ልብ በምን ዓይነት መልክ ይገልጡልናል? እነዚህን ሰዎች እንደራስ መውደድ ማለት ምን ይመስላል?

2. 1ኛ ነገሥት 8፡41-43፣ ኢሳይያስ 56፡6-7፣ ማርቆስ 11፡17
እግዚአብሔር በሌላ ሐገር ስለሚኖሩ ወይም ስለመጻተኞች ጸሎት ምን ዓይነት ስሜት ይሰማዋል? ዓለም አቀፍ ሰዎችን እንደ ፕሮጀክት ሳይሆን በእግዚአብሔር አምሳል እንደተፈጠሩ የከበሩ ሰዎች አድርጎ ማየት የሚቻለውስ እንዴት ነው?

3. ሐዋ 1፥8፤8፡27-35፤35-39
በእነዚህ ቦታዎች ካለው ከጌታ ትዕዛዝ አንጻር በሐገራችን ያሉ ዓለም አቀፍ ሰዎችን ስልታዊ በሆነ መንገድ የምንደርሳቸው እንዴት ነው?

4. ማርቆስ 5፡14-20፣ ዮሐንስ 4፡39-42
ከእነዚህ ጥቅሶች ኢየሱስ ለመጻተኞች ወይም ለውጪ ሀገር ሰዎች ስላለው አመለካከት ምን እንማራለን?

5. 1ኛ ተሰሎንቄ 2፡7-8፡-
ወንጌልን ብቻ ሳይሆን የገዛ ሕይወትን ለሌሎች ስለማካፈል ከጳውሎስ ምሳሌነት ምን እንማራለን? ይህ እኛ ስላነሳነው ጉዳይ፡ ዓለም አቀፍ ሰዎችን ከመድረስ ጋር እንዴት ይገናኛል?

# ተግብሩ

1. ስለ ዓለም አቀፍ ሰዎች ያላችሁ አስተሳሰብ የእግዚአብሔርን ቃል ካጠናችሁ በኋላ እንዴት ተለወጠ?

## ለተግባራዊ ህይወት ጠቃሚ ሐሳቦች

1. በሚቀጥለው ጊዜ ከምታገኙት ዓለም አቀፍ ሰው ጋር ንግግር ጀምሩ (ምናልባት ይህ ከእነርሱ ይልቅ ለእናንተ እንግዳ ነገር ሊሆን ይችላል)፡፡ ራሳችሁን አስተዋውቁና ስለ ባህላቸው አንዳንድ ጥያቄ አቅርቡላቸው፡ ፡ ከንግግራችሁ በኋላ ሌላም ጊዜ ተገናኝታችሁ የበለጠ ለመጨዋወት ይፈልጉ እንደሆነ ጠይቋቸው፡፡ ከመለያየታችሁ በፊት ስልክ ቁጥራቸውን መቀበል አትርሱ፡፡
2. አዳዲስ ዓለም አቀፍ ሰዎችን ለማግኘት ወደምትችሉባቸው ቦታዎች፡ ለምሳሌ ዓለም አቀፍ ሬስቶራንቶች፡ የመዝናኛ ቦታዎች ወይም ወደ ሱፐር ማርኬቶች ሂዱ፡፡
3. የተዋወቃችኋቸውን አዳዲስ ሰዎች ወደ ማንኛውም የምትሠሩት ሥራ ጋብዟቸው፡፡ ወደ ገበያ ስትሔዱ፣ ወደምትማሩበት ቦታ፣ ወደ ሥራ ቦታችሁ፣ ወደ ሠርግ፣ ወደ ቤታችሁ፣ ወዘተ ሊሆን ይችላል፡

## እውነተኛ ታሪክ

ሳሙኤል የተባለ ቻይናዊ ዓለም አቀፍ ተማሪ የተዋወቅሁት ወደ ቻይና ካደረግሁት የአጭር ጊዜ ጉዞ መልስ በኋላ ነበር፡፡ እየተገናኘን ቅርጫት ኳስ መጫወትና አብሮ መብላት ጀመርን፡፡ አንድ ቀን ምሳ እየበላን ሳለ ሳሙኤል ከእኔ ጋር አብሮ ወደ ቤተክርስቲያን ለመሔድ እንደሚፈልግ ገለጸልኝ፡፡ እኔም በጣም ደስ ብሎኝ መስማማቴን ገለጽኩለት፡፡ ከዚያም ሳሙኤል ስለመጽሐፍ ቅዱስ አንዳንድ ጥያቄዎችን መጠየቅ ጀመረ፡፡ እኔም የተቻለኝን ያህል ለጥያቄዎቹ መልስ መስጠትና ከእግዚአብሔር ቃል ማስረዳት ሞከርኩ፡፡

አንድ ቀን አብረን ሳለን ወንጌልን በግልጽ እንድነግረው እግዚአብሔር እንደመራኝ ስለተረዳሁ ነገርኩት፡፡ በዚያን ምሽት ሳሙኤል በመረዳት ክርስቶስን ተቀበለ፡፡ ዓለም አቀፍ ሰዎችን በእንግድነት መቀበል የጠየቀኝ ነገር ቢኖር ራስን ማቅረብና መታዘዝን ነው፡፡ እግዚአብሔር ዓላማውን በእኔ በኩል ሲያከናውን የእኔ ተግባር ራሴን እነሆ ብዬ መስጠት ብቻ ነበር፡፡ ሌላ ምንም ነገር አላደረግኩም፡፡ -- ሐድሰን

ሐድሰን በጣም ግሩም ሰው ነው! ወደ ክርስቶስ እንድሳብ ያደረገኝ አመለካከቱና ማንነቱ ነበር፡፡ ሁልጊዜ አብረን ጊዜ እንድናሳልፍ ይጋብዘኝ ነበር፡፡ በእያንዳንዱ ምሽት አንድ ነገር እናደርግ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ በየጊዜው ስለ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ስለ ኢየሱስ፣ ጥያቄ እጠይቀው ነበር  ሐድሰንም መልሱን ያሳየኝ ነበር፡፡ ሐድሰን ወዳጄ ስለሆነ በጣም ደስ ብሎኛል፡፡ -- ሳሙኤል

1. እንደ ተቀባይ ማገልገል የምትጀምሩት እንዴት ነው?

2. ስለዚህ ነገር ራሳችሁን ለማን ተጠያቂ ታደርጋላችሁ?

# ጸልዩ


## ሐየ.ሙ.ኀ.ቡ.ሂ፡- ሙስሊም

ሙስሊሞች በአብዛኛው በኢንዶኔዥያ፣ በሰሜን አፍሪካ፣ በመካከለኛው ምስራቅና በአውሮፓ ይኖራሉ፡፡

### የሙስሊም ሕዝቦች እምነት

- አላህ ብለው በሚጠሩት በአንድ አምላክ እና መሐመድ ደግሞ የእርሱ የመጨረሻ ነብይ ነው ብለው ያምናሉ፡፡
- አንድ ሰው ሲሞት በሕይወት ዘመኑ የፈጸመው ምልካም ሥራ ከክፉ ሥራው የበለጠ ካመዘነ፡ ወደ ገነት ይገባል ብለው ያምናሉ፡፡
- ኢየሱስን እንደ መልካም ነብይ ያከብሩታል፡ ነገር ግን አምላክ ነው ብለው አያምኑም፡፡





## በሱዳን ማስሪያ የሚኖሩት ባጋራ

574,000 ሕዝብ /0 % ወንጌላውን

አብዛኛዎቹ ባጋራዎች በሰሜን ሱዳንና በአዋሳኝ ግዛቶች ውስጥ የሚኖሩ አርብቶ አደሮች ናቸው፡ ፡ ባጋራዎች የግማሽ እንቁላል ቅርጽ ባለው; በክብ ቅርጽ በተሠሩ ቀላል ድንኳኖች ውስጥ ይኖራሉ፤ በምሽት ጊዜ ከብቶቻቸውም ወደ እነዚህ ድንኳኖች ይገባሉ፡፡ የባጋራ ጎሳ ሰዎች በሙሉ "አምስቱን የእስልምና ምሶሶዎች" በታማኝነት የሚጠብቁ ሙስሊሞች ናቸው ለማለት የሚቻል ሲሆን፣ አብዛኛዎቹ ወንዶችና አንዳንዶቹ ሴቶች ወደ መካ የጸሎት ጉዞ ያደርጋሉ፡፡

በእያንዳንዱ መንደር ወሳኙ አካል ወንዶች የተሰባሰቡበት ጉባኤ ሲሆን፣ ለከብቶቻቸው እንክብካቤ በማድረግ በኩል ሁሉም ወንዶች ተሳታፊ ይሆናሉ፡፡ በቁጥር አናሳ የሆኑ እርሻ ያላቸው፣ በመዝራትና መከር በመሰብሰብ የሚተዳደሩ አርሶ አደር ማኅበረሰቦችም አሉ፡፡ በባጋራ ማኅበረሰብ፣ ባልተለመደ መልክ ለቤተሰቡ የሚያስፈልገውን ገቢ ለማግኘት የሚደክሙት ሴቶቹ ናቸው፡፡ ከብቶቻቸውን በማለብ፣ ወተትና የወተት ተዋጽኦን በመሸጥ ገንዘብ ያገኛሉ፡፡ ያገባች ሴት ድንኳንም ሆነ ለቤቷ የሚያስፈልገው



ቁሳቁስ ባለቤት ናት፡፡ የባጋር ጎሳ ወንጌል በሚገባ ያልደረሰው ሕዝብ ነው፡፡ አዲስ ኪዳን በቋንቋቸው የተተረጎመ ሲሆን፣ አንዳንድ የሬዲዮ ፕሮግራሞችም አሏቸው፡፡ ነገር ግን ሰዎቹ ለእስልምና እምነት የተሰጡ በመሆናቸው፣ ወደ ጌታ የመጡት ባጋሮች በጣም ጥቂቶች ናቸው፡፡ በተጨማሪም የአኗኗር ዘይቤያቸው የዘላንነት ባህርይ ስላለው እነርሱን ለመድረስ ለሚሠማሩ ሚሲዮናዊያን አስቸጋሪ አድርጎታል፡፡

## ምልጃ

1. ባጋራዎች በአካል ዘላን ቢሆኑም እንኳን በኢየሱስ ክርስቶስ መንፈሳዊ ቤትና እረፍት እንዲያገኙ ጸልዩ፡፡ መልካሙን እረኛ ወደ ማወቅ እንዲመጡና የእርሱን ድምጽ እንዲከተሉ ጸልዩ፡፡
2. ጌታ ሆይ ዓኔን በመከፈት እውነትን በመፈለግና ስለአንተ ለማወቅ እየጣሩ ካሉ ዓለም አቀፍ ተማሪዎች ጋር አገናኘኝ
3. አባት ሆይ ከማገናቸው አለም አቀፍ ተማሪዎች ጋር ስገናኝ እንደ እርሱ እንድንሆንና ግንኙነትም ከእነርሱ ጋር እንዳተናከር ብረታትን ስጠኝ፡፡



# ትምህርት 6
## የእግዚአብሔር ሥራ:- መሔድ

አንዳንዶች ከቤተክርስቲያን ደወል ድምጽ ሳይርቁ መኖርን ይመኛሉ፤
እኔ ግን በገሃነም ግዛት የህይወት አድን ሱቅ ከፍቸ መኖር እፈልጋለሁ፡፡ ሲ.ቲ. ስተድ

## ዝግጅት

### ወደ ዓለም ዳርቻ

በትምህርት ሁለት ለወንጌል ተደራሽ ያልሆኑ ብዙ ሕዝቦች እንዳሉ ተመልክተናል፡፡ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ውስጥ የባህል ዘለል አገልጋዮች ሆነው ባልተደረሱ ሕዝቦች መካከል ለማገልገል ራሳቸውን የሚሰጡ ብዙዎች ያስፈልጉናል፡፡ ያለንን ማንኛውንም ክህሎት፣ ተሰጥኦ፣ ችሎታ፣ ሙያ ወይም ስብዕና ባልተደረሰው ዓለም ውስጥ ለማገልገል ወደ ፊት ብናመጣው እግዚአብሔር ማንኛችንንም ይጠቀምብናል፡፡

የሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች እውነት ወይም ሐሰት መሆናቸውን በማክበብ ግለጹ፡፡ መልሶቻችሁ ትክክል መሆናቸውን ካመሳከራችሁ በኋላ አብረው የሚሔዱትን ጥቅሶች አንብቡ፡፡

እውነት ወይም ሐሰት
ለባህል ዘለል አገልግሎት የሚሠማሩ ሰዎች የቋንቋ ስጦታ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

እውነት ወይም ሐሰት
ያልተከፈለ የትምህርት ዕዳ ያለበት ሰው የባህል ዘለል አገልጋይ መሆንን ባያስበው ይሻላል፡፡

እውነት ወይም ሐሰት
አብዛኛዎቹ የባህል ዘለል አገልጋዮች ዲግሪያቸውንና የሥራ ልምዳቸውን ሊጠቀሙበት አይችሉም፡፡

እውነት ወይም ሐሰት
በባህር ማዶ ካለው ተፈላጊ ችሎታ የተነሳ፡ የባህል ዘለል አገልጋይ ለመሆን አንድ ሰው ቤተክርስቲያን ተካይ ወይም የእንግሊዘኛ መምህር መሆን ይገባዋል፡፡

እውነት ወይም ሐሰት
ትዳርና ቤተሰብ ላለው ሰው፡ ቤተሰቡ ወደ ባህር ማዶ ለመሔድ የማይፈልግ ከሆነ ምንም ነገር ቢሆን እዚያው በሐገሩ መቆየት አለበት፡፡

እውነት ወይም ሐሰት
አንድ ሰው ካላገባ ባህል ዘለል አገልጋይ በመሆን ወደ ባህር ማዶ መሔድ አይገባም፡፡

እውነት ወይም ሐሰት
እግዚአብሔር የባህል ዘለል አገልጋይ ሆኖ ለመሔድ የሚፈልግን ሰው፡ ወደ አደገኛ ወይም ወደ አስቸጋሪ ቦታ አይመራውም፤ አንድ ሰው ወደ እንዲህ ዓይነቱ ቦታ ለመሔድ የሚፈልግ ከሆነ ይህ የእግዚአብሔር ምሪት አይደለም፡፡

እውነት ወይም ሐሰት
ድጋፍ ማሰባሰብ ያልቻለ ሰው ወይም ለማድረግ የማይወድ ከሆነ መሔድ ለእንደዚህ ዓይነቱ ሰው የሚሆን አይደለም፡፡

**ሚሲዮናዊ የሚለውን ስታስቡ ወደ አእምሮአችሁ የሚመጣው ምንድን ነው? የባህል ዘለል አገልጋይ ሆኖ ማገልገልን ስታስቡ በጣም የሚያስፈራችሁ ምንድን ነው?**

ሠ ፡ሠ ፡ሠ ፡ሠ ፡ሠ ፡ሠ ፡ሠ ፡ሠ -፡ህየመ

### [ባህል ዘለል ተላኪ]

ባህል ዘለል ተላኪ ማለት፡ ከራስ ባህል ትልቅ ልዩነት ባለው ባህል ውስጥ ያሉ ሰዎችን በኢየሱስ ክርስቶስ እውነት ለመድረስ የሚሠራ ሰው ነው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ እንዲህ ዓይነቱ ተግባር በባዕድ ወይም በሩቅ ሐገር በመስክ ላይ የሚደረግ ስራ ነው፡፡

### [ግንባር ቀደም ተላኪ]

ግንባር ቀደም ተላኪ ቤተክርስቲያን በሌለችበት ሕዝብ ውስጥ፡ ከሐገሬው ሰዎች መካከል አማኝ ማህበረሰብን ለማቋቋም የሚፈልግ የባህል ዘለል ሠራተኛ ነው፡፡

# የሚሲዮናዊ ጥሪ

በሮበርት ኢ. ስፒር

የሚሲዮናዊነት ጥሪ ምን ያካትታል? ሰዎች ይህንን መጠየቃቸው ጥሩ ምልክት ነው፡፡ በመጀመሪያ የሚሲዮናዊነት ሥራ፡ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር ብቻ የተያያዘ እንደሆነ እንደሚያስቡ ያመለክታል፡፡ ሁለተኛም ሕይወታቸው በሌላው፣ እነርሱን ለመምራት መብት ባለውና ጥሪውን በሚጠብቁት አካል የተያዘ እንደሆነ ማመናቸውን ያመለክታል፡፡

እነዚህን ሁለት ነገሮች በምንናገርበት ጊዜ ጥያቄውን በመደገፍ ሊባሉ የሚቻሉ ነገሮችን ሁሉ ያልን ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም አብዛኛውን ጊዜ ክርስቲያናዊ ባልሆኑ ምክንያቶች ጥያቄው ስለሚጠየቅ ነው፡ ፡ ለምሳሌ ያህል እዚህ ሰሜን አሜሪካ ሀገር ውስጥ ክርስቲያኖች ወደ ሚሽን መስክ መሔድ የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን አጥብቀው የሚጠይቁን ያህል፡ በአንድ ሙያ ላይ ፈቃዱ ስለመሆኑ ብዙም አዎንታዊ ማረጋገጫ  ሳይፈልጉ ይሰማራሉ፡፡ ነገር ግን በምን ላይ ተመስርተው እንዲህ ዓይነቱን ልዩነት መፍጠር ይችላሉ? ክርስትና መላው ሕይወትንና አገልግሎትን ለእግዚአብሔር መሰጠትን የሚጠይቁትን ነው፡፡ ማንም ሰው ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ የሆነን ነገር ማድረግ የለበትም፡፡ አንድ ሰው አንድን የሕይወት መንገድ ለመጓዝ በሚያስብበት ጊዜ፡ እግዚአብሔር ፈቃዱ ከሆነው ነገር ውጭ አንዳችም ያነሰ ወይም የበለጠ ነገር ለማድረግ መፈለግ የለበትም፡፡

ሰዎች በተለያዩ አገልግሎቶች መካከል የልዩነት መስመር የሚያሰምሩ ከሆነ፡ ምን ዓይነት የአመክንዮ ሕግ ነው አንድን  ሰው በአረማውያን መካከል ሔዶ በሚሲዮናዊነት ለመኖር መለኮታዊ ማረጋገጫ የሚያስፈልገው፡ ነገር ግን በቀላሉ በክርስቲያኖች መካከል ሕይወትን ለማሳለፍ ያን ያህል መለኮታዊ ማረጋገጫ የማያስፈልገው ነገር አድርገው እንዲያስቡ የሚመራቸው? ሰዎች ለማንኛውም ጉዳይ ልዩ ጥሪ የሚያስፈልጋቸው ከሆነ፡ የራሳቸውን ተግባር ለማከናወን፣ በሕይወታቸው ዘመን ሁሉ ጥሩ ጊዜ እንዲኖራቸው፣ ለመኖር የሚመች

ቦታ ለመምረጥ፣ ገንዘብ ለመሰብሰብና፡ የራሳቸውን ምኞት ለማርካት ካሰቡ ለዚህም ልዩ ጥሪ እንዲኖራቸው ያስፈልጋቸዋል፡፡

የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ለዓለም ሁሉ እንዲሰበክ

## ብዙዎቻችን የምንፈልገው የሚሲዮናዊነትን ጥሪ አይደለም፤ የምንፈልገው ግፊትን ነው፡፡

በክርስቲያኖች ላይ አጠቃላይ የሆነ ግዴታ ተቀምጦአል፡ ፡ የእግዚአብሔር አጠቃላይ ጥሪ በሕይወታችን ተግባራዊ እንዲደረግ ለእኔና ለእናንተ ልዩ ጥሪ አያስፈልገንም፡ ፡ ከዚህ ሀላፊነታችን ነጻ ለመሆን ልዩ ጥሪ ያስፈልገናል፡ ፡ በሌላ አነጋገር፡ እያንዳንዳችንን ነጻ የሚደርገን ልዩ ነገር ከሌለ በስተቀር፣ ሕይወታችንን ለዓለም ለመስጠት ተቀባይነት ያለው ግዴታ ተጥሎብናል፡፡

ሚሲዮናዊ ለመሆን ልዩ ጥሪ ማግኘት ያስፈልጋል የሚባለው ነገር ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የሚጻረር ነው፡ ፡ "ወደ ዓለም ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ" የሚል ትዕዛዝ አለን፡፡ ይህ ለተለዩ ሰዎች ነው እንላለን፡፡ "እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ወደ እኔ ኑ" ይላል፡፡ "ይህ ማለት ለእኔ ነው" እንላለን፡፡ ትእዛዙን በተመለከተ ለእኛ ስለመሆኑ ልዩ የሆነ መለኮታዊ ምሪት ያስፈልገናል እንላለን፡፡ በረከቱን በተመለከተ ግን እኛን የሚመለከት ስለመሆኑ አንዳችም መለኮታዊ ማረጋገጫ አንጠይቅም፡፡ ለክርስቲያን በተሰጠ ግዴታና በረከቶች መካከል የልዩነት መስመር ለማስመር መብቱን የሰጠን ማን ነው? በረከቶቹ ለእያንዳንዱ ክርስቲያን ሁሉ የሚሰሩ፣ ግዴታዎቹ ግን የእያንዳንዱ ህሊና ውሳኔ እንደሆነ አድርገን ለመውሰድ ማን መብት ሰጠን?

መሠረታዊ ከሆኑት ከአመክንዮ ሕግና ከእውነተኛ ዳኘነት መርሆዎች ጋር የሚጋጭ ነው፡፡ ይህን ወደ አንድ ወገን ያዘመመ አካሔድ ይዘን የሕይወታችንን ሌሎች ክፍሎች በስርዓት እንመራለን ብለን ማሰብ አንችልም፡ ፡ ብዙዎቻችን የምንፈልገው የሚሲዮናዊነትን ጥሪ አይደለም፤ የምንፈልገው ግፊትን ነው፡፡

በወንዝ ዳርቻ ቆሜ ትንንሽ ልጆች በውሃው ሲወሰዱ እየተመለከትኩ፣ አንድ የሕግ ባለስልጣን መጥቶ እነዚህን ልጆች እንድታድን በዚህና በዚያ ሕግ መሠረት ትዕዛዝ ተሰጥቶሃል ብሎ ወረቀት እንዲሰጠኝ አያስፈልገኝም፡፡ በዚያ ቆሜ እነዚህን ህጻናት ለማዳን እየቻልኩ አንዳንድ የሕግ ስርዓት እስኪፈጸምና እኔም በሕግ የተደነገገ ሥልጣን እስኪሰጠኝ ድረስ የምጠብቅ ከሆነ፡ ራሴን መጥላትና ከንቱ ሰው አድርጌ መመልከት ይገባኛል፡፡

አንድ ሰው መርህን በዕለት ተዕለት የሕይወት ጉዳዮቻችን ውስጥ በሚተገበር መልኩ እንድናደርገው  ሲነግረን፣

በምንጠላውና በምንጸየፈው ማብቂያ የሌላቸውን መዘዞች በሚያስከትል መልኩ ለምን እናደርገዋለን? ለደቂቃ ያህል የተራበውን ዓለም ጨኸት አዳምጡ፡፡ ለአንዲት ሰዓት የመከራውን ስሜት ተካፈሉ፡፡ ለጥቂት ጊዜ ስለ ሰቆቃው እዘኑ፡፡ ይህም ነገር በጎረቤታችሁ ያለው፣ ወይም በጎዳና ላይ ስትጓዙ የምታገኙት፣ ወይም ደግሞ በሕይወት ውስጥ በየትም ስፍራ የሚያጋጥማችሁ ሰው የሚፈልገው ነገር እንደሆነ ተረዱ፡፡

የሚሲዮናዊነትን ጥሪ በተመለከተ የሚያስገርሙ ስህተቶች፣ የተሳከሩ አመለካከቶችና የተሳሰቱ እምነቶች አሉ፡፡ እንዲያውም ብዙዎቻችን የምንፈልገው የሚሲዮናዊነትን ጥሪ አይደለም፤ የምንፈልገው ግፊትን ነው፡፡ እንዲያውም ብዙዎቻችን ጥሪ የሚባለው ነገር ቢመጣም እንኳን ስምተን አናውቅም፡፡ ወደ ሚሲዮናዊ ሥራ ከመግባታችን በፊት አንድ ሰው መጥቶ በሃይል የሚያስገድደን ያስፈልገናል፡፡

እያንዳንዳችን በየስፍራው ስለኢየሱስ ክርስቶስ ሰምተው የማያውቁ ሰዎችን በወንጌል ለመድረስ ሕይወታችንን፣ ጊዜችንንና ንብረታችንን እንድንሰጥ አጠቃላይ ግዴታ የተጣለብን ነን፡፡ እንዳይመለከተን የሚያደርግ በንጹህ ህሊና በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት የሚቀርብ፡ ደግሞም ምክንያታችንን እርሱ እንደተቀበለው እርግጠኛ የምንሆንበት ማስረጃ ከሌለን በስተቀር፡ የመሔድ ግዴታ አለብን፡፡

"ሕይወታችሁን በገዛ ፈቃዳችሁ መምራት አለባችሁ ነው የምትለን?" ብላችሁ ትጠይቁ ይሆናል፡፡ አይደለም! እንዲያውም እኔ በትክክል እየተቃወምኩት ያለው ነገር ይህን ነው፡፡ አሁን በትክክል እያደረግን ያለነውም ይህንን ነው፡፡ እግዚአብሔር መጥቶ፡ በሌላ መንገድ እንድንሔድ እስከሚያስገድደን ድረስ ሕይወታችንን በገዛ ፈቃዳችንና እኛ በፈለግነው መንገድ እየመራናት ነው ያለነው፡፡ እኔ እየጠየቅሁ ያለሁት፡ እግዚአብሔር በየትኛውም በኩል አንድ ልዩና ግላዊ መንገድ እስኪገልጽልን ድረስ ሕይወታችንን በኢየሱስ እጅ ላይ አድርገን እርሱ ለቤተክርስቲያን ግልጽ አድርጎ ባሰመረላት መንገድ እንሂድ ነው፡፡



# ተወያዩ

1. 2 ቆሮ 5፥18-20
እግዚአብሔር ለክርስቲያኖች ሁሉ የሰጠው ምንድን ነው? ምን እንድንሆንና እንድናደርግ ነው የጠራን?

2. ራእይ 5፥9 2ጴጥ 3፥9
በእነዚህ ጥቅሶች መሠረት፡ የእግዚአብሔር ሕዝብ መሔድ የሚኖርበት ለምንድን ነው?

3. ሰዎች ሚሲዮናዊ ላለመሆን የሚሰጧቸው ዋና ምክንያቶች ምንድን ናቸው? የሚያቀርቧቸው ነገሮች ምክንያቶች ይመስሏችኋልን?

4. ሮሜ15፥19-21
ወንጌል ባልደረሰባቸው ሕዝቦች መካከል ቤተክርስቲያን የሚሄዱት 10% ያህሉ ብቻ እንደሆኑ በትምህርት ሁለት ውስጥ ተምረናል፡፡ ጳውሎስ ባሕል ዘለል ሠራተኞች ያላቸው ዐላማ ያለው ለምንድነው የእግዚአብሔር ዓለም አቀፋዊ ዐላማ እንዲፈፀም ይህ ምን ያህል ወሳኝ ነው?

5. ሮሜ 110፥ 13-15
በእነዚህ ጥቅሶች መሠረት የሚያስፈልገው ምንድን ነው? **ለምን ወሳኝ ነው ?**

# ተግብሩ



1. አብዛኛው የኢየሱስ ደቀመዛሙርት ከኢየሩሳሌም ውጪ ከ1200-3300 ኪሎ ሜትር ባለው ርቀት ላይ ሰብከዋል ፤ ሰማዕት ሆነዋል እነርሱም እስከ ኢትዮጵያ ደቡባዊ ክፍል ወደ አብዛኛው ሰሜናዊ አፍሪካ ወደ ሮማ ግዛቶች ወደ ብሪታኒያ ደሴቶች ወደ አረብ አገሮች ወደ ፋርስ እንዲሁም እስከ ሕንድ ድረስ ተጉዘዋል ወንጌል ለዓለም ሁሉ ተሰብኮ ለማየት ከደቀመዛሙርት መሥዋዕትነት አንጻር ምን ያህል መሥዋዕትነት ለመክፈል ፈቃደኞች እንደሆናችሁ አስቡ

2. በወንጌል ያልተደረሰው ሕዝብ ወደ ኢየሱስ ሲመጣና እርሱን ሲያመልክ እንድታዩ ራሳችሁን ከመስጠት የሚያግዳችሁ ነገር ምንድን ነው?

## ለተግራዊ ሕይወት ጠቃሚ ሐሳቦች

1. በሚቀጥለው ዓመት አጭር የሆነ ስልታዊ ጉዞ ለማድረግ አቅዱ፡፡
2. በየዕለቱ ለእግዚአብሔር የትም ቦታ ለመሄድ፣ በማንኛውም ጊዜ፣ አንድ ነገር ለእርሱ ለማድረግ ለእርሱ ምሪት ራስህን ክፍት አድርግ፡፡
3. ባህል ተሻግሮ ለረዥም ጊዜ የሔደ ወይም ሔዶ የነበረ አንድ ሰው ፈልግና ታሪኩን እንዲነግርህ ጠይቀው፡፡

## እውነተኛ ታሪክ

የዓለም አቀፍ ክርስቲያኖች ሴሚናር ላይ ተገኝተን እግዚአብሔር ለሕዝቦች ያለው የልብ ኃሳብ ምን እንደሆነና ስለኢየሱስ ለመስማት የሚችሉበት መንገድ የሌላቸው ሰዎች ስታቲስቲክስ ምን እንደሚመስል ተማርን፡፡ የሰማነው መረጃ በውስጣችን ገብቶ ተቀመጠ፡፡ የመጀመሪያ ቤታችንን ገና መግዛታችን ነበረ፤ የምንወደው ሥራም ነበረን፤ ገና ልጅ መውለዳችንም ነበር፡፡ እግዚአብሔር በሕዝቦች መካከል ይታወቅ ዘንድ ፍላጎቱን የሚያሳይ አንዳችም ነገር በእኛ ህይወት ውስጥ የሚታይ ነገር ግን አልነበረም፡፡

የመጀመሪያውን ግንዛቤ ካገኘን ከሃያ ወራት በኋላ፡ የሁለት ዓመትና የዘጠኝ ወራት ሕጻናት ልጆቻችንን ይዘን ወደ ምስራቅ እስያ ተጓዝን፡፡ ብዙ ሰዎች አእምሮአችን በትክክል የማያስብ መሰላቸው፤ አንዳንዶችም ጀግኖች አድርገው አዩን፤ ለእኛ ግን የገባን ነገር ቢኖር ለመታዘዝ ፈቃደኛ መሆናችን ብቻ ነበር፡፡ ከአሥራ ሁለት ዓመታት ፍሬያማ አገልግሎት በኋላ አራት ተጨማሪ ልጆቻችንን (ሶስቱ የማደጎ ልጆቻችን ናቸው) ይዘን ቤተሰባችን ሁሉ ወደ አፍሪካ መጣ፡፡ እኛ ልዩ ነገር አድርገናል ማለት አይደለም፤ ምክንያቱም በእግዚአብሔር ስልት እርሱ በጣም በሚፈልገው ቦታ ተገኝተን እርሱን መከተላችን የሚያስገኘውን እርካታ የትኛውም ምድራዊ ደስታ ሊያስገኘው አይችልም፡፡
ሲአን እና አማንዳ

1. ከዚህ ትምህርት የተነሳ ማድረግ የምትፈልገው አንድ ለውጥ ምንድን ነው?

2. በዚህ ጉዳይ ራስህን ተጠያቂ የምታደርገው ለማን ነው?


# ሐየ.ሙ.ኅ.ቡ.ሂ፡- ቡዲሐስቶች

ቡድሒስቶች በአብዛኛው የሚኖሩት በደቡብ ምስራቅ እስያ፣ በቻይና እና በጃፓን ነው፡፡

## እምነቶቻቸው

- መከራ የሚመጣው ከምኞት የተነሳ ነው ብለው ያምናሉ፡፡
- መከራን ለማስቆም በጥሞና በማሰላሰልና ደጋግሞ በመፈጠር ምኞትን ማስወገድ ይኖርብናል ይላሉ፡፡
- የመጨረሻው ግብ መከራ ወደሚያቆምበትና እኔነት መኖሯን ወደምታበቃበት ወደ ፍጹም በረከትና ልዩ የመገለጥ ልምምድ መድረስ ነው፡፡





## ቡታንግፖ የሁታን ሕዝብ

20 500/ 0% ወንጌላውያን

ሁታን ቡድሃ እምነት ተከታዮች መንግሥት ስትሆን የምትገኘውም በሂማሊያ ተራሮች ላይ ነው ፡፡ ሁታን ማለት የመብረቅ ድራጎን ምድር ማለት ነው ፡፡ ቡምታንግፖ ከ7ኛው ክፍለ ዘመን በፊት በቡምታንግ ሸለቆ በማዕከላዊ ቡትሐን የነበረ ሥፍራ ነው፡፡ የቡምታንግፖ ሕዝቦች ገበሬዎች ናቸው፡፡ ሩዝና ስንዴ አምራች ሲሆኑ ቤት እንስሳትን ያረባሉ፡፡

በመቶዎች የሚቆጠሩ ነዋሪዎች በየሳምነቱ ጃካር ወደ ተባለ ገበያ ለመሸጥና ለመግዛት ይሄዳሉ ቡምታንግፖ የነበራቸው ለ1200 ዓመታት ነው፡፡

የነበራቸውን እምነትም እልተለወጠም እምነታቸው ዱዲዝም ሲሆን የአካባቢያቸውን አማልክትንም በየዕለቱ ዕጣን በማጠን ያመልኳቸዋል ፡፡ ባሕታውያን የማኅበረሰብ መሪዎች ናቸው የቡምታንግፖ ነው ባሕታዊያኑ ለአገሬው ልጆች ሁሉ ስም የማውጣት ኃላፊነት አለባቸው፡፡

አንድ ታዋቂ በሆነው የበዓል ወቅታቸው ባሕታውያኑ በየመንደሩ በመሄድ ጉዳት የሚያደርሱ መናፍስትን ያስወጣሉ፡፡ ከዚህም በኋላ የመንደሩ ሰው ሁሉ ተሰብስቦ 10 ጫማ ርዝመት ባለውና በእሳት በነደደበት ደጋን መሰል እንጨት በመዝለል ለአዲሱ ዓመት ራሳቸውን ማንጻት ሥርዐት ያደርጋሉ፡፡



# ምልጃ

1. በከፍታ ላይ ያለህ እግዚአብሔር  ለቡምታንግፖ ሕዝቦች ከመከራ የመውጫው ብቸኛ መንገድ በክርስቶስ ሰላምና ህይወት እንደሆነ ግለጥላቸው ለእነዚህ ሕዝቦች ኢየሱስ ተአምራታዊና ህይወትን ለዋጭ በሆነ መንገድ ግለጥላቸው፡፡

2. አባት ሆይ ከክፉ መናፍስት በእውነት ነጻ ልታወጣቸውና ከኃጢአታቸው ልታነጻቸው ምትችለው አንተ ብቻ እንደሆንክ ግለጥላቸው፡፡

3. ወየመከሩ ጌታ ሆይ አዲስ የመከር ሠራተኞችን በኃይል አስታትቀህ ወንጌል ወዳልደረሰባቸው ቦታዎች ማለትም እንደ ሁታንና ቡምታንግፖ ወደ መሳሰሉት አስቸጋሪ ሥፍራዎች እንድትልክ እንለምንሃለን፡፡



# ትምህርት 7
# የእግዚአብሔር ሥራ፡- ማስተባበር

ከእግዚአብሔር ታላቅ ነገርን ጠብቁ፡ ለእግዚአብሔር ታላቅ ነገርን ለማድረግ ሞክሩ፡፡
ዊሊያም ኬሪ

## ዝግጅት

### ሌሎችን ወደ ተግባር መጥራት

ባለፉት ስድስት ትምህርቶች፡ የእግዚአብሔርን ዓለም አቀፋዊ ዓላማ፡ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረቱንና፡ ይህንን ዓላማ ለማሳካት የቀረውን ሥራ አይተናል፡፡ ታላቁ ተልዕኮን ከግብ ለማድረስ ሁላችንም ልንለማመዳቸው የምንችላቸውን አራት የዓለም አቀፍ ክርስቲያን ልማዶችን ተመልክተናል፡፡ እነርሱም መጸለይ፣ መላክ፣ መቀበልና፣ መሔድ ናቸው፡፡ ይህ የመጨረሻው ትምህርት ደግሞ አምስተኛው ልማድ፣ ማለትም ማስተባበር ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡ በረከትን ተቀብላችኋል፤ አሁን ደግሞ ያንኑ በረከት ወደ ሌሎች የምታስተላልፉበት ጊዜ ነው፡፡

የሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች እውነት ወይም ሐሰት መሆናቸውን በማክበብ ግለጹ፡፡ መልሶቻችሁ ትክክል መሆናቸውን ካመሳከራችሁ በኋላ አብረው የሚሔዱትን ጥቅሶች አንብቡ፡፡

እውነት ወይም ሐሰት
አስተባባሪ መሆን የሚፈልግ ሰው፡ ሰዎችን በቶሎ መግባባት የሚችል መሆን አለበት፡፡

እውነት ወይም ሐሰት
ማስተባበር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኝ ነው፡፡

እውነት ወይም ሐሰት
ማስተባበር የሚፈልግ ሰው መደበኛ ሥልጠና መውሰድ አለበት፡፡

እውነት ወይም ሐሰት
ማስተባበር ሐቆችን ማካፈል ነው፤ ማንም ሰው የአንተን ታሪክ ለመስማት አይፈልግም፡፡

እውነት ወይም ሐሰት
ማስተባበር እያንዳንዱን ሰው ወደ ሌላ ሐገር ሔዶ እንዲኖር ለማድረግ መሞከር ነው፡፡

እውነት ወይም ሐሰት
የባህል ዘለል አገልግሎት ውስጥ ለመግባት ከሚፈልጉ ከመቶ ሰዎች ውስጥ በተግባር በረጅም የሚሸን ስራ ላይ የሚሰማራው አንድ ሰው ብቻ ነው፡፡

እውነት ወይም ሐሰት
ብዙ ሐብት ስለሌለ ማስተባበር ከባድ ተግባር ነው፡፡

እውነት ወይም ሐሰት
አስተባባሪዎች የሚባሉት የሚጸልዩ፣ የሚሔዱ፣ የሚልኩና የሚቀበሉ እና ሌሎችም እንዲቀላቀሏቸው የሚጋብዙ ናቸው፡፡

ስለ ማስተባበር ስታስቡ ወደ አእምሮህአችሁ የሚመጣው ምንድን ነው? እነዚህ ነገሮች እግዚአብሔር ሕዝቦችን ለመድረስ ከሚፈልገው የልቡ ሸክም ጋር እንዴት ይዛመዳሉ?

---

መልስ፡- ሐ፤ እ፤ ሐ፤ ሐ፤ ሐ፤ እ፤ ሐ፤ እ

### [አስተባባሪዎች]

አስተባባሪዎች የሚባሉት፡ ሌሎች ዓለም አቀፋዊ ራዕይ፣ ናፍቆት እና ስልት እንዲኖራቸው የሚያስታጥቁና በታላቁ ተልዕኮ ውስጥ ያላቸውን ስልታዊ ድርሻቸውን እንዲረዱ የሚያግዙ ናቸው፡፡

### [ዓለም አቀፍ ክርስቲያኖች]

ዓለም አቀፍ ክርስቲያኖች እግዚአብሔር ለዓለም ያለውን የልቡን ኃሳብ ተረድተው ማንኛውም የሚያደርጉት ነገር፡ የትም ቦታ ቢኖሩ፣ ምንም ዓይነት ስራ ቢሰሩ፡ እግዚአብሔር በሕዝቦች መካከል ከብሮ ለማየት እንዲችሉ ሕይወታቸውን ስልት በተሞላ ሁኔታ የሚኖሩ ናቸው፡፡

# ሞዴል መሆንና መጋበዝ

## በቲቶ ኤች

አንድ በጣም ያስደሰታችሁና የወደዳችሁት፣ ከዚህም የተነሳ ለሌሎች ልትነግሩት የፈለጋችሁት ነገር ኢጋጥሞአችሁ ያውቃል? ፊልም፣ አዲስ የኤሌክትሮኒክ መሳሪያ፣ እረፍት ያሳለፋችሁበትና የጎበኛችሁት ቦታ፣ ወይም ደግሞ አንድ ማድረግ የምትወዱት ጥሩ ልምድ ሊሆን ይችላል፡፡ አንድ የምትወዱት ነገር ካለ ለሌሎች መንገር የማይቀር ነው፡፡ አንተን ደስ እንዳሰኘህ ሌሎችም እንዲደሰቱ ትፈልጋላችሁ፡፡ ለእናንተ በተሰማችሁ ትልቅ ስሜት ተነሳስታችሁ እናንተ የምትወዱትን ያንን ነገር እነርሱም እንዲገዙ፣ ፊልምም ከሆነ እንዲያዩ፣ ወይም ሌሎች ሰዎች ልማዳችሁን እንዲጋሩአችሁ ልታሳምኗቸው ሞክራችኋል? እንዲህ ካደረግህ እንኳን ደስ አላችሁ፤ አስተባብራችኋል ማለት ነው፡፡

ሰዎች የእኛን ደስታ ሲካፈሉ ደስ እንደሚለን፣ እግዚአብሔርም የእርሱን ልብ ደስ የሚያሰኘው ነገር እኛን ሲያስደስተን ደስ ይለዋል፡፡ አባታችን ወንጌልን ሰምተው ወደማያውቁ ሰዎች መድረስ ይናፍቃል፤ እኛም ይህን ደስታውን አብረን እንድንካፈለው ይፈልጋል፡፡ ያልተደረሱትን ለመድረስ ሰዎችን ማስተባበር ማለት፣ ሰዎች የእግዚአብሔርን ሚሽን ለመቀላቀልና የዓለም አቀፍ ክርስቲያን የሕይወት መንገድን ተቀብለው ለማደግ በሚንተጉታቸው መልኩ የእግዚአብሔርንና የእኛን ደስታ ማካፈል ነው፡፡ አስተባባሪዎች፣ ሌሎች አማኞች ዓለም አቀፍ ክርስቲያኖች እንዲሆኑ የሚረዱ ናቸው፡፡ ሰዎች የእግዚአብሔርን ዓለም አቀፋዊ ሚሽን ተመልካች ከመሆን ወጥተው፣ በታላቁ ተልዕኮ ውስጥ ስልታዊ ሚናቸውን በሕይወት በመተግበር ንቁ ተሳታፊዎች እንዲሆኑ ማድረግ ነው፡፡ ስናስተባብር በዓለም ዙሪያ ሁሉ ያሉ አማኞች፣ ወንጌል ያልደረሳቸውን ሕዝቦች ሁሉ እንዲያዩ እናደርጋለን፡፡

ሌሎች ዓለም አቀፍ ክርስቲያኖች እንዲኑሱ ለማድረግ የተሻለው መንገድ፡ በመጀመሪያ ያንን የሕይወት መንገድ ሞዴል ሆኖ ማሳየት ነው፤ ከዚያም ሌሎች ይህንን መንገድ እንዲቀላቀሉ መጋበዝ ነው፡፡ ለሕዝቦች ስትጸልዩ ሌሎችም አብረዋችሁ እንዲጸልዩ ጋብዟቸው፡፡ ሚሲዮናዊያንን በገንዘብ ስትደግፉና የሚያበረታታ ማስታወሻ ስትጽፉ ሌሎችም እንዲሰጡና ማስታወሻ እንዲጽፉ ጋብዙ፡፡ በሌላ ባህልና ሃይማኖት ውስጥ ያለውን ዓለም አቀፍ ሰው ወደ ሕይወታችሁ ስትጋብዙና ስትቀበሉ ወዳጆቻችሁም ከእናንተ ጋር ሆነው ይህንኑ እንዲያደርጉ ጋብዟቸው፡፡

ሞዴል በመሆንና ሌሎችን በመጋበዝ በኩል ኢየሱስ ምሳሌያችን ነው፡፡ እርሱ የኖረው ሕይወት ሆን ብሎ የሚያደርገውና በዓላማ የሚከውነው ነበር፤ ሌሎችም ያንኑ እንዲያደርጉ ጋብዟቸዋል፡፡ ሞዴል መሆንና መጋበዝ የማስተባበር ዋነኛ ልብ ስለሆነ፡ ሁላችንም አስተባባሪዎች መሆን እንችላለን፡፡ የቢዝነስ ባለሙያዎች ብንሆን፣ በቤት ውስጥ ያለን እናቶችና የቤት እመቤቶች፣ ተማሪዎች፣ ወጣት፣ በመካከለኛ ዕድሜ ያለ ጎልማሳ ወይም አዛውንት፣ ተግባቢዎች ወይም ቁጥቦች፣ ሁላችንም ለዓለም አቀፍ ክርስቲያኖች የሕይወት መንገድ ሞዴል ለመሆንና ሌሎች እንዲቀላቀሉን ለመጋበዝ መንገድ አናጣም፡፡

በምግብ ሰዓት የመጸለይ ልምድ ካላችሁ አብራችሁ ስለሚሲዮናዊያንና ስላልተደረሱ ሕዝቦች መጸለይ ትችላላችሁ፡፡

ሌሎችም ያንኑ እንዲያደርጉ መጋበዝና ውጤታማ ጸሎት እንዲጸልዩ የሚረዳቸውን ጽሑፎች በመስጠት ማዘጋጀትስ ምን ያስቸግራል? በሰንበት ትምህርት ቤት ክፍል ውስጥ ወይም በአንድ ንዑስ ቡድን ውስጥ በመሳተፍ ላይ ካላችሁ፡ ቡድኑ የተወሰነ ጊዜ ወስዶ የሚሽንን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረቶች እና ዓለማችን የሚገኝበትን ሁኔታ እንዲመለከት መጠየቅ ትችላላችሁ፡፡ የዓለም ዜና አንብባችሁ ወይም ሰምታችሁ ከሆነ አንዳንድ ወቅታዊ ኹነቶች ያልተደረሱ ሕዝቦች ላይ እያሳደረ ስላለው ችግር መነጋገርም ይቻላል፡፡



# አስተባባሪዎች ሌሎች አማኞች ዓለም አቀፍ ክርስቲያኖች እንዲሆኑ የሚረዱ ናቸው፡፡

ከወዳጆቻችሁ ጋር ወጣ ብላችሁ ምግብ የምትበሉ ከሆነ፡ ወደ አንድ የሌላ ብሔር ምግብ ቤት በቋሚነት ሂዱና እዚያ ካሉት የምግብ ቤቱ ሰራተኞች ጋር ወዳጅነትን መስርቱ፡፡ እነዚህ እንግዲህ በዙሪያችን ባሉ ሰዎች ላይ የዓለም አቀፍ ክርስቲያኖችን ተጽዕኖ የምናሳድርባቸው አንዳንድ መንገዶች ናቸው፡፡ በእርግጠኝነት እነዚህ ነገሮች ከምቾት ስፍራችሁ ገፍተው ያወጧችሁ ይሆናል፤ ነገር ግን ሆን ብላችሁ ለእግዚአብሔር ዓለም አቀፋዊ ሚሽን ቅድሚያ የምትሰጡ ከሆነ ሞዴል መሆንና መጋበዝ የማንነታችሁና የተግባራችሁ አንድ አካል እየሆኑ ይመጣሉ፡፡

በዓመት አንድ ሰው ዓለም አቀፍ ክርስቲያን እንዲሆን መርዳት ከቻላችሁ፣ አስተባባሪ ናችሁ ማለት ነው፡፡ አስር ሰዎች መርዳት ከቻላችሁ፣ ወይም ሃምሳ ወይም አምስት መቶ፣ አስተባባሪ ናችሁ፡፡ ማስተባበር ብዙ ዓይነት መልክ ይኖረዋል፤ አብዛኛውን ጊዜ መጀመር የሚቻልበት ስፍራ አንተ ዓለም አቀፍ ክርስቲያን በሆናችሁበት በዚያው ሒደት ውስጥ በማለፍ ነው፡፡ በጣም ጠቃሚው ነገር እግዚአብሔርን መፈለግ፣ ዕቅድ ማቀድና ሆን ብሎ ማድረግ ነው፡፡

በምታስተባብርበት ጊዜ ልታስታውሳቸው የሚገቡ ሶስት ነገሮች፡-

1. አስተባባሪዎች ከሰዎች ጋር ግንኙነት ፈጣሪዎች ናቸው፡፡ ከሰዎች ጋር ልብ ለልብ መገናኘት ስንችል ውጤታማ መሆን ይቻላል፡፡ ሰዎች ዓለም አቀፍ ክርስቲያን ሆነው ለማደግ ማድረግ ያለባቸውን ልንነግራቸው እንችላለን፤ ነገር ግን የተሻለ የሚሆነው በሒደቱ ውስጥ አብረን የምንጓዝ ከሆነ ነው፡፡ የምታደርጉትን ነገር ሆን ብላችሁና አስባችሁበት አድርጉ፤ ጥያቄዎችንም ለመመለስ ራሳችሁን አዘጋጁ፡፡ ፍርሃታቸው እንዲወገድ እርዷቸው፤ እያደጉ ሲሔዱም አበረታቷቸው፡፡

2. አስተባባሪዎች ጠቃሚ ምንጮችን ይጠቀማሉ፡፡ ሰዎች ዓለም አቀፍ ክርስቲያን ሆነው እንዲያድጉ የሚያግዟቸውን ምንጮች እንዲጠቀሙ መርዳት እንችላለን፡፡ የሚሽን መጽሐፍ፣ አጫጭር ቪዲዮዎች፣ በሚሽን ኤጀንሲዎች የተዘጋጁ የጸሎት በራሪ ጽሑፎች፣ ወይም ድረ-ገጾች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ምን ዓይነት የመረጃ ምንጮች እንዳሉ እውቀት ይኑራችሁ፡፡ እናንተ መረጃዎቹ ሁሉ ሊኖሯችሁ ያስፈልጋል ማለት አይደለም፤ የት እንደሚገኝ ማወቁ ግን ጠቃሚ ነው፡፡ ለመጀመር ያህል በገጽ 58 ላይ የቀረበውን የመረጃ ምንጮችን ዝርዝር ተመልከቱ፡፡

3. አስተባባሪዎች ትሑታን ናቸው፡፡ አስተባባሪ ስንሆን አብያተ ክርስቲያናትን፣ መጋቢዎችን ወይም ሰዎችን ስህተታቸውን ለማሳየትና በሚገባ እንዳልሰሩ ለመናገር አይደለም፡፡ አስተባባሪ የሆንነው ለማበረታታት፣ ለማነሳሳትና በታላቁ ተልዕኮ ተሳታፊነት ያለው አኗኗር ምን እንደሚመስል ሞዴል ለመሆን ነው፡፡ አስተባባሪዎች ለአጥቢያ ቤተክርስቲያናት በረከት መሆን አለባቸው፡፡ ከተቻለ የማስተባበር እቅዳችሁን በአጥቢያ ቤተክርስቲያናችሁ ስር ሆናችሁ፣ ከመሪዎቻችሁ በረከትና የእነርሱን አስተዋጽኦ ተቀብላችሁ፣ እግዚአብሔር የከፈተላችሁን በሮችም ሁሉ እየተጠቀማችሁ ተንቀሳቀሱ፡፡

አስተባባሪነታችሁ ወዴየትኛውም አቅጣጫ ሊመራችሁ ቢችል፡ ከሆነ ቦታ ግን እንድትጀምሩት እጋብዛችኋለሁ፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስን ከሞት ያስነሳው መንፈስ በእናንተም ውስጥ ይኖራል! የጥንቷን ቤተክርስቲያን በኢየሩሳሌም፣ በይሁዳና በሰማርያ እስከ ምድርም ዳርቻ ድረስ ምስክር እንዲሆኑ ያደረጋቸው መንፈስ በእናንተ ውስጥ ይኖራል (ሐዋ 1:8)! እግዚአብሔር የዓለምን ሕዝቦች ሁሉ ይወዳል፡፡ ብዙ ሰዎችን ወደ ታላቁ ተልዕኮ እንዲቀላቀሉ ማድረግ ወደምትችሉበት ደረጃ ሊያሳድጋችሁ ይጓጓል፡፡ ማስተባበርን የሕይወታችሁ ክፍል እንድታደርጉት እጋብዛችኋለሁ፡፡ ሒዱ አስተባብሩ ብዬ እጋብዛችኋለሁ፡፡

# ተወያዩ

1. ሌሎቻችን በማስተባበር አኳያ የምታስቡትና የሚሰማሁ ነገር ምንድነው ደስተኛ ነህ? ተስፋ ቆርጠሃል? እግጠኛ አይደለህምን? መተማመን አለህ ...ወዘተ ?

2. ማቴ 4፥19፤1ቆሮ 11፥1
እነዚህ ክፍሎች ኢየሱስና ጳውሎስ እግዚአብሔርን ከማስተባበር አንጻር ምን ያስገነዝባሉ?

3. ሉቃስ 24፥45-48
በትምህርት አንድ ላይ እንደተመለከትነው ኢየሱስ በዚህ ክፍል ውስጥ ከማስተባበር አኳያ ሞዴል የሆነው እንዴት ነው? ኢየሱስ ደቀመዛሙርት እንዲገነዘቡት የሚፈልገው ነገር ምን ነበር?

4. ማቴ 9፥36-38፤ ሉቃ 10፥1-2
በትምህርት ሁለት ላይ እንደተመለከትነው በእነዚህ ክፍሎች ውስጥ ከማስተባበር አኳያ ሞዴል የሆነው እንዴት ነው ኢየሱስ ስለጠፉትና ስለመከሩ ሠራተኞች የተናገረው እንዴት ነው? ምን ተግባራዊ ድርጊቶችን ኢየሱስ አመላከተ?

5. ሮሜ 10፥ 14-15
በእነዚህ ክፍሎች የምታይዋቸው ሚናዎች ምንድን ናቸው? ማስተባበር ከዚህ ክፍልና ሚናዎች ጋር የሚጣጣመው እንዴት ነው?

6. ራእይ 5፥9፤ 7፥9-10
እነዚህ ሁለት ክፍች ማስተባበር በሚለው መጽሀፍ ውስጥ ያነበብናቸው ጥቅሶች ነበሩ፡፡ አሁን ክፍሎቹን ስትመለከቱ ምን ሐሳቦች ይኖራችኋል? እነዚህን ጥቅሶች ከማስተባበር አኳያ እንዴት ልትጠቀሙባቸው ትችላላችሁ?

# ተግብሩ

## እውነተኛ ታሪክ

እግዚአብሔር ለዓለም ያለውን የልቡን ኃሳብ የሚያሳየውን ራዕይ ባገኘሁ ጊዜ፡ በ10/40 መስኮት ውስጥ ባልተደረሱት መካከል ያለውን በጣም አስፈላጊ ነገር ማየት ጀመርኩ። ሌሎችም እንዲበረቱና እንዲቀላቀሉ ማድረግ ፈለግሁ፤ ስለዚህም እግዚአብሔር ለዓለም ያለውን ልብ የሚሳዩ ጥቅሶችን በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኔ ውስጥ ማካፈል ጀመርኩ። ከአዳዲስ ዓለም አቀፍ ተማሪዎች ጋር በምገናኝበትም ጊዜ ሌሎች ልጃገረዶችን ወደ ጥናት እንዲመጡ እጋብዛቸው ነበር። ልጃገረዶቹም ሕዝቦችን የመድረስ ራዕዩን ስለተቀበሉ ወደ ሌሎችም ማስተላለፍ ጀመሩ። እግዚአብሔር ቤተክርስቲያኑን ሲነካና ወንጌልን ወደ ዓለም ዳርቻ ለመውሰድ ሲያነሳሳ ማየት በእውነት ታላቅ ነገር ነው! ጄኒ

## ለተግባራዊ ሕይወት ጠቃሚ ሐሳቦች

ማስተባበር ሌሎች ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር አለም ዐቀፋዊ ዐላማዎች መጥራት ሲሆን አሁን እየሠራችሁት ወዳለሁ አለም አቀፋዊ ሥራዊች ሰዎች በመገበዝ መጀመር እንደሚቻል አስተውሉ።

1. ወደ ዓለም አቀፍ የሕይወት ዘይቤ ለመምጣት ከምን ዓይነት ክርስትያን ቡድን ጋር ግንኙነት ጀምራችኋል ? ለምሳሌ የእሁድ ትምህርት ተማሪዎች ናቸው? የማኅበረሰብ ቡድን ናቸው? መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን ናቸው

2. ግንኙነት በጀመርከው ቡድን ውስጥ የሥራ አጋርህ ልታደርገው ምትችለው ሰው አለን? ይህንን ቡድን ለማስተባበር ራእይህንና ግብህን ማካፈልን አብረን መፀለይን እና ማስተባበርን አትዘንጋ።

3. ፀሎት
የመጀመሪያው ቀላል ደረጃ ሰዎች ወንጌል ላልደረሳቸው ሰዎች በዙሪያችን ላሉ የአለም አቀፍ ሰዎችና ሚሲዮናውያን እንዲፀልዩ ማስተባበር ነው። በቡድኑ ዘንድ ዓለም አቀፋዊ ፀሎጵን የምታስተዋውቁት እንዴት ነው?

4. መላክ
ቡድኑን ወደ ሚሲዮናዊያን በአንድ ላይ በመላክ እንዲንከባከቧቸው ለማድረግ የምትጠቀሚቸው አንዳንድ የማስተባበር መንገዶች ምንድን ናቸው?

5. መልካም አቀባበል
በሥራው ገና ተሳታፊ ያልሆናችሁ ጀማሪዎች ከሆናችሁ በተለየ ባህል ውስጥ ያለን አንድን ሰው እንዴት ወዳጃችሁ ልታደርጉት ትችላላችሁ?

# የአለም አቀፍ ክርስቲያን የሕይወት ዘይቤ ዕቅድ

”ማስተባበር” በሚለው መጽሐፍ ውስጥ ያሉ ትምህርቶችን ስናልፍ ስለ እግዚአብሔር ቃል ስራ ዓለም ስለ ፀሎት ስለ መላክ ስለ መልካም ኣባበል ስለመሁድ እና ስለ ማስተባበር የተማራችሁትን መሠረት በማድረግ ከግል ሕይወታችሁ ጋር እንዳዛመዳችሁት እርግጠኛ ነን፡፡ በመማር ሂደት ውስጥ ሁለንተናዊ የሆነ አቀራረብ ራስ ልብንና እጅን ያጠቃልላል፡፡

1 ራስ

ስለ ሚሽን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረትና ስለ ዓለም ሁኔታ ከተማራችሁት ውስጥ ምን ዕውቀት ገንዛቤና አቋም አገኛችሁ?

2 ልብ

በተለይ ከሌላ ባሕል ወይም ወገን ሆነው ኢየሱስ የሚለውን ስም ያልሰሙ ሰዎችን በመውደድ ያላችሁ ፍቅር እያደገ የመጣው እንዴት ነው ?

3 እጆች

የተማራችሁትን ነገር ከየዕለት ሕይወታችሁ ጋር በማዋሐድ እንዴት ወደ ተግባር ትለውጡታላችሁ? በቡድን ስትወያዩ ማስታወሻ ያዙ፡፡

4 ፀሎት

ለመንግስታትና ለሚሲዮናውያን ያለማቋረጥ ለመፀለይ የምትችሉባቸውን አንዳንድ መንገዶችን ጥቀሱ፡፡

5 መላክ

ለመንግስታትና ለሚሲዮናውያን ያለማቋረጥ ለመፀለይ የምትችሉባቸውን አንዳንድ መንገዶችን ጥቀሱ፡፡

6 መልካም አቀባበል

በሌላ ባሕልና እምነት ውስጥ ላሉ ሰዎች ወዳጅ ወይም አገልግይ ልትሆኑ የምትችሉባቸው አንዳንድ መንገዶች ዘርዝሩ፡፡

7 *መሄድ*

እግዚአብሔር እየመራህ ያለው ለአጭር ወይስ ለረጅም ጊዜ ምን ይሰማሃል? ስለ መልካም አጋጣሚዎች ከማን መነጋገር ትችላለህ?

8 ማስተባበር

ክርስቲያናዊ የሆነውን ዓለም አቀፋዊ ተፅእኖን በሌሎች ላይ ማምጣትን ለመጀመር ምን ምን እርምጃዎችን ትወስዳለህ?

9 *መማር*

ስለ እግዚአብሔር ቃል ስለ ሥራ ባለህ ዕውቀት አኳያ ባለማቋረጥ ማደግህ መልካም ነው፡፡ በገፅ 59 ላይ ቀጣይ እርምጃዎች በሚለው ርእስ ሥር አንዳንድ ሐሳቦችንና የመረጃ ምንጮች ይገኛሉ ብዙ ለመማር ምን ልታደርግ ትችላለህ?

# ፀሎት

በእግዚአብሔር አለም አቀፋዊ ዐላማ አኳያ ራስህን ሚና ለመጫወት ዕቅድ ይኖር ይሆናል፡፡ ስለሆነም ለእግዚአብሔር እስከተወሰነ ጊዜ ራሳችንንና መንገዶቻችንን አሳልፈህ ስጥ፡፡

## ምልጃ

1. አባት ሆይ እነዚህን ልምምዶች በሕወታችን ውስት በቅደም ተከተል ለማካተት ኃይልና ብርታትን ስጠን፡፡

2. አባት ሆይ እነዚህ ልምምዶች ሕግና ሥርዓት ሳይሆን በአንተ ዓለም አቀፍ ዐላማ ውስጥ በደስታ በምንሳተፍባቸው እንዲሆኑ ሐሳባችንንና ልባችንን በአንተ ላ እንድናደርግ እርዳን፡፡

3. አባት ሆይ! በምድር ሁሉ ሕዝብ ዘንድ ስምህን እንድትቀድሰውና እንድታከብረው እንፀልያለን በሰማይ እንደሆነው ሁሉ በምድር ላይ ባሉ ሕዝቦች ሁሉ ላይ መንግስት እንድትመጣና ፈቃድህ እንዲፈፀም እንፀልያለን፡፡



# APPENDIX & RESOURCES

## እንኳን ደስ አላችሁ!

ዓለም አቀፍ ክርስቲያን ለመሆን በመንገዱ ላይ ናችሁ! የበለጠው ደግሞ እግዚአብሔር እስከ ዓለም ዳርቻም. . . ለሌሎች በረከት እንድትሆኑ፣ ዕቅድ አዘጋጅቷል!

ግባችን ምን ያህል ሰዎች አንድ ተጨማሪ መጽሐፍ አጥንተው ጨረሱ የሚለውን ለማየት አይደለም፡፡ ተማሪዎች ያሉበት መኖሪያዎች፣ አብያተ ክርስቲያናትና በዓለም ዙሪያ ያሉ ቡድኖች ለእግዚአብሔር ዓለም አቀፋዊ ዕቅድ ንቁ እንዲሆኑ ነው፡፡ አሁን የእናንተ ቡድን ይህንን ፍለጋ የተባለውን አጥንቶ አጠናቋል፤ አሁን ደግሞ ለአንተ የምናቀርበው ጥያቄ እናንተም ሌሎች ጥቂት አማኞችን አሰባስባችሁ ይህንን የጥናት ጽሑፍ እንድታጠኑት ነው፡፡ ምንም ዓይነት ልምድም ሆነ የምስክር ወረቀት አያስፈልግም፤ በእናንተ በኩል የሚያስፈልገው ነገር ጥቂት ወዳጆችን አሰባስቦ ውይይቱን ለመምራት ፈቃደኝነት ብቻ ነው፡፡ በዓለም ላይ ተጽዕኖ እንድታመጡ እግዚአብሔር እንዲጠቀምባችሁ እንወዳለን!

## Resources

የሚሽን አስተባባሪ ማዕከል
mobilization.org

The Traveling Team
thetravelingteam.org

የፀሎት ድረ -ገፆች
globalprayerdigest.org

Campus Ministry Tooday
campusministryorg

WEAVE
weavefamily.org

Operation World
operationworld.org

የተጠናከሩ መረጃዎች
missionfrontiers.org

William Carey Library
missionbooks.org

Student Volunteer Movement 2
svm2.org

Ask A Missionary
askamissionary.com

6 Ways to Reach God's World
6ways2reach.org

# የሚሽን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት

## [ብሉይ ኪዳን]

### በመጀመሪያ
ዘፍጥረት 1:28

### ለኖህ የተሰጠ ትዕዛዝ
ዘፍጥረት 9:1

### የባቢሎን ግንብ
ዘፍጥረት 11:1-9

### ለአብርሃም ቤተሰብ የተሰጠ ተስፋ
ዘፍጥረት 12:1-3፣ 26:4.፣ 28:14

### ዘጸአት
ዘጸአት 9:15-16፣ ኢያሱ 4:23-24

### አሥርቱ ትዕዛዛት
ዘዳግም 4:5-6

### የሰሎሞን ጥበብ
1ኛ ነገሥት 4:34

### መቅደሱ
1ና ነገሥት 8:41-43

### ዳዊትና ጎልያድ
1ኛ ሳሙኤል 17:46

### ሲድራቅ፣ ሚሳቅ፣ አብድናጎ
ዳንኤል 3:28-29

### ዳንኤልና የአንበሶቹ ጉድጓድ
ዳንኤል 6:25-27

### ስለኢየሱስ የተነገሩ ትንቢቶች
ኢሳይያስ 49:6

### መዝሙራት
2:8
9:11
18:49
22:27-28
45:17
46:10
47:1-9
57:9
66:1-8
67:1-7
72:8-11
77:13-14
86:9
96:1-13
98:1-9
99:1-3
105:1
108:1-5

## [አዲስ ኪዳን]

### ምስክርነት ለሕዝቦች ሁሉ
ማቴ 24፥ 14
ማር 13፥10
ማር 16፥15
ሉቃ 24፥46-47

### ታላቁ ተልዕኮ
ማቴ 28፥ 18-20

### የአህዛብ የፀሎት ቤት
ማር 11፥17

### ኢየሱስ እንደተላከ የተላከ
ዮሐ 20፥21

### እስከ ዓለም ዳርቻ ምስክር መሆን
ሐዋ 1፥8

### ለአህዛብ ብርሃን መሆን
ሐዋ 13፥46-47

### በአህዛብና በአይሁድ መካከል ልዩነት
የለም
ሐዋ 15፥7-19
ኤፌ 3፥6-8

### አህዛብ ሁሉ የሆነ መታዘዝ
ሮሜ 1፥5
ሮሜ 16፥25-27

### ክርስቶስ ባልተሰበከበት ቦታ እርሱን
መስበክ
ሮሜ 15፥15-27

### ሕዝቦች ሁሉ የተባረኩ ናቸው
ገላ 3፥8

### ሰው ሁሉ እንዲድን የእግዚአብሔር
ፈቃድ ነው
1ጢሞ 2፥3-4

### ስለ አለም ሁሉ ኃጢአት የሆነ የማስተባበሪያ ኃጢአት
1ዮሐ 2፥2

### ከነገድ ከቋንቋ ና ከሕዝብ
ራእ 5፥9-10
ራእ 7፥9-10

# [ለተግዳሮት የተዘጋጁ መሆን]

mobilzation.org/challenges

የ 7 ቀን ተግዳሮት ለአንድ ሳምንት በየዕለቱ አምስት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ላይ ምልክት አድርግ እነዚህ ምንባቦች ትኩረት የሚያደርጉት እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ሁሉ ባለው ልብ ላይ ሲሆን እኛም እንዴት ተሳታፊ እንደምንሆን ያስተምራሉ፡፡


## የ30 ቀን ተግዳሮቶች

አንድ ሳምንት በየዕለቱ በአምስት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ምልክት አድርግ እነዚህ 150
ናና ክፍሎች የእግዚአብሔርን ዓለም አቀፋዊ ዕቅድና ዐላማ ከዘፍጥረት እስከ ዮሐንስ ራዕይ በጥልቀት እንድንገነዘብ ያደርጋል።
ሂዱ አስተባብሩ እና ፍለጋ በሚሽን ማዕከል የተዘጋጁ ጽሑፎች ናቸው፡፡

# መስኮቱን አካፍሉ

ለሰዎች ስለዓለም አቀፍ ክርስቲያኖች የሕይወት መንገድ ለማሳወቅ፡ መስኮቱን መጠቀም በጣም ጥሩ መንገድ ነው፡፡ ቀለል ያለ ስዕል በመጠቀም የእግዚአብሔርን ቃል፣ የእግዚአብሔርን ዓለም እና የእግዚአብሔርን ሥራ ልታሳዩአቸው ትችላላችሁ፡፡ መስኮቱ በቃል ያጠናችሁትን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችና ሐሙጎቡሂ የተባለውን ምህጻረ ቃል ለማብራራት ይረዳል፡፡ እንዴት እንደሚሠራ ተመልከቱ፡፡

**ለምሳሌነት የተሞላ መስኮት**




**እንዴት እንጀምር**

*መሸጋገሪያ 1*: ባልንጀራችሁ ስለ ዓለም አቀፍ ክርስቲያን የሕይወት መንገድ ሰምቶ ያውቅ እንደሆነና ዓለም አቀፍ ክርስቲያን ማለት ምን እንደሆነ የተረዳውን በመጠየቅ ጀምር፡፡

**ተግባር :** አራት ክፍሎች በውስጡ የያዘ መስኮት ሥሩ፡፡ ለጊዜው የመስኮቱን ውስጠኛ ክፍል ምንም ነገር አትጻፉበት፡፡

**ማብራሪያ**: ይህንን የመስኮት ስዕል በመጠቀም የእግዚአብሔርን ዓለም አቀፋዊ ዓላማና እንደ ክርስቶስ ተከታዮች የእኛን ሚና በተሻለ መገንዘብ እንደሚቻል አብራሩ፡፡

| | |
|---|---|
| የእግዚአብሔር ቃል | የእግዚአብሔር ዓለም |
| የእግዚአብሔር ሥራ | |

*መሸጋገሪያ 2*: እንዲህ ብላችሁ ተናገሩ፡፡ “ነገር ግን የእግዚአብሔርን ዓለም አቀፋዊ ዓላማ ለመረዳትና በተቻለ መጠን በጣም ስልታዊ በሆነ መንገድ ከእርሱ ጋር ለመሥራት በሶስት አቅጣጫ ግንዛቤ ሊኖረን ያስፈልጋል፡፡ እነዚህም ሶስት አቅጣጫዎች . . .”

**ተግባር :** የላይኛውን የግራ የመስኮት ክፍል “የእግዚአብሔር ቃል”፣ የላይኛውን የቀኝ ክፍል ደግሞ “የእግዚአብሔር ዓለም”፣ እንዲሁም የታችኛውን የግራ ክፍል “የእግዚአብሔር ሥራ” ብላችሁ ጻፉበት፡፡ ለጊዜው የታችኛውን የቀኝ ክፍል ባዶ አድርጋችሁ ተውት፡፡

**ማብራሪያ**

ዓለም አቀፍ ክርስቲያን ማለት ስለ ክርስትና ህይወቱ ዓለም አቀፋዊ አመለካከት የያዘ ሰውና ሶስቱን አቅጣጫዎች፣ ማለትም የእግዚአብሔር ቃል፣ የእግዚአብሔር ዓለም እና የእግዚአብሔር ሥራ የሚሉትን ተረድቶ ሕይወቱንም በእነዚህ መሠረት የሚመራ ሰው ማለት ነው፡፡

| | |
|---|---|
| 1 | **የእግዚአብሔር ቃል**<br>ዘፍ 12፡1-3፣ መዝ 46፡10፣ ኢሳ 49፡6<br>ማቴ 28፡19-20፣ እና ራዕይ 7፡9 |

*መሸጋገሪያ* 3: ከእግዚአብሔር ቃል በመጀመር ባልንጀራችሁ ስለ ሚሽን ወይም ስለ "ሕዝቦች የሚናገር ማንኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ያውቁ እንደሆነ ጠይቁ፡፡ የሚያውቁትን ጥቅት ከመስኮቱ በአንድ ወገን ጻፉ፡፡

**ተግባር**: መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ለሕዝቦች ስላለው ፍቅር የሚናገረው ብዙ ጥቅሶች እንዳሉት አሁን ለባልነጀራችሁ ተናገሩ፡፡ እኛ ግን በአምስት ክፍሎች ላይ ትኩረት እናድርግ፡፡ የእግዚአብሔር ቃል የሚል ስም በሰጣችሁት የመስኮቱ ክፍል ውስጥ ቁጥር 5ን ጻፍ፡፡ ከዚያም የሚከተሉትን ዘርዝሩ፡፡ ዘፍ 12፡1-3፣ መዝ 46፡10፣ ኢሳ 49፡6፣ ማቴ 28፡19-20 ራዕይ 7፡9፡፡

**ማብራሪያ**: ጥቂት ደቂቃ ወስዳችሁ እያንዳንዱ ጥቅስ የእግዚአብሔርን ዓለም አቀፋዊ ዓላማ እንዴት እንደሚያሳይ በመግለጽ አምስቱን ጥቅሶች አብራሩ፡፡ ስትገልጹ መጽሐፍ ቅዱስ በእጃችሁ ቢኖር መልካም ነው፡፡ ሆኖም ጥቅሶቹን በልባችሁ እንድትይዟቸው እናበረታታችኋለን፡፡

| | |
|---|---|
| 2 | **የእግዚአብሔር ዓለም**<br>ሐይማኖት አልባ፣ ሙስሊም፣ ጎሳዊ<br>ቡድሒስቶች እና ሒንዱዎች |

*መሸጋገሪያ* 4:

**ተግባር**: የእግዚአብሔር ዓለም የሚል ስም የተሰጠው የመስኮቱ ክፍል ውስጥ "5" ቁጥርና፣ ከጎኑ ደግሞ ሐሙጎቡሂ የሚለውን ምህጻረ ቃል ጻፉ፡፡ እንዲህ የመሰለ ነገር ተናገሩ፡፡ ይህንን ምህጻረ ቃል ለማስታወስ ከቻላችሁ፣ በዓለም ላይ ያሉትንና 90 በመቶ የሚሆኑትን ያልተደረሱ ሕዝቦች ለማስታወስ ቻላችሁ ማለት ነው፡፡ ከስዕሉ የታችኛውና የግራ ክፍል በውጪ በኩል 10 ቁጥር፣ በላይኛውና የግራ ክፍል በውጪ በኩል ደግሞ 40 ቁጥር መጻፍ ትችላላችሁ፡፡ እነዚህን ሁለት ቁጥሮች በመጠቀም 10/40 መስኮትን፣ ማለትም አብዛኛዎቹ ያልተደረሱ የዓለም ሕዝቦች የሚገኙበትን መልክዓ ምድራዊ ክፍል ለመግለጽ ትችላላችሁ፡፡


**ማብራሪያ**: አምስቱን ታላላቅ ክፍሎች አብራሩ፡፡ ሐማኖት አልባዎች፣ ሙስሊሞች፣ ጎሳዊ፣ ቡድሒስቶች እና ሒንዱዎች፡፡ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ በእነዚህ ላይ ትኩረቶቻውን ያደረጉት ጥቂቶች ብቻ እንደሆኑ ግለፁ፡፡ በእነዚህ ቦታዎች ላይ የተሰማሩት ሚሲዮናውን ቁጥር 10 በመቶ የሚሆኑት ብቻ ሲሆኑ፣ በገንዘብ በኩል ደግሞ 0.1 በመቶ የሚሆነው ብቻ በእነዚህ ቦታዎች ላይ ይውላል፡፡ በ1 ሚሊዮን ያልተደረሱ ሰዎችና በክርስቲያን ሠራተኞች መካከል ያለውን ጥመርታ ጠቁሙ (ገጽ 14 ተመልከቱ)፡፡ ለምሳሌ በ1 ሚለዮን ሒንዱዎች መካከል 2 ሠራተኞች ብቻ አሉ፡፡ ከዚህ በተቃራኒ አብዛኛው የዓለም ቤተክርስቲያን ጊዜ፣ ሃብትና ስጦታ የሚሔደው በተደረሱና ጠንካራ የክርስትና ሕይወት ባለበት ቦታ መሆኑን አብራሩ፡፡ የተደረሱና ያልተደረሱ የሚሉትን መጠሪያዎች ግልጽ ማድረግን መዘንጋት የለባችሁም፡፡

| | |
|---|---|
| 3 | **የእግዚአብሔር ሥራ**<br>መሔድ፣ መላክ፣ መቀበል፣<br>ማስተባበር እና መጸለይ<br>**5 ልምዶች** |

*መሸጋገሪያ* 5: በእግዚአብሔር ቃል መሠረት፣ ከእግዚአብሔር ዓለም ፍላጎት አንጻር፣ አለም አቀፍ ክርስቲያኖች በእግዚአብሔር ሥራ ውስጥ ይሰማራሉ፡፡ ይህንንም 5ቱን የዓለም አቀፍ ክርስቲያኖች ልማዶች በማድረግ ያከናውናሉ፡፡

**ተግባር**: የእግዚአብሔር ሥራ በሚለው የመስኮቱ ክፍል 5 ልማዶች ብላችሁ ጻፉ፡፡ ከዚያም አምስቱን ልማዶች ዘርዝሩ፡፡ መጸለይ፣ መላክ፣ መቀበል፣ መሔድ እና ማስተባበር ናቸው፡፡

**ማብራሪያ**: እያንዳንዱን ልማድ ምን ማለት እንደሆነ በመግለጽ አብራሩ፡፡ እነዚህን ነገሮች ምርጫዎች ከማለት ይልቅ ልማዶች ለማለት የፈለግነው ለምን ይመስላችኋል በማለት ባልንጀራችሁን ጠይቁ፡፡ አንዱን ወይም ሁለቱን ብቻ መርጠን ሳይሆን ሁሉንም መለማመድ እንደምንችል ደግሞም እንዳለብን አብራሩ፡፡የዓለም አቀፍ ክርስቲያኖችን ልማድ ለመተግበር ምን እያደረጋችሁ እንደሆነ ከገለፃችሁ በኋላ፣ ባልንጀራችሁም እነዚያኑ ልማዶች የራሱ እንዲያደርግ ጠይቁ፡፡




*መሸጋገሪያ 6፡* እስካሁን የእግዚአብሔርን ቃልና እርሱም የዓለም ሕዝቦችን ለመድረስ እንደሚፈልግ ተመልክተናል፡፡ የእግዚአብሔርንም ዓለም ተመልክተን የሚቀረው ሥራ ምን እንደሚመስል የተሻለ መረዳት አግኝተናል፡፡ አሁን ደግሞ አምስቱን የዓለም አቀፍ ክርስቲያኖች ልማዶች ተመልክተናል፡፡ አሁን ራሳችንን በሀቀኝነት የምንመዝንበት ጊዜ ነው፡፡

**ተግባር**: በመጨረሻው የመስኮቱ ክፍል፡ የጥያቄ ምልክት ጻፉና በሁለቱም የመስኮቱ ጎኖች በኩል የሰው ስዕል ሥሩ፡፡ በአንዱ በኩል ክርስቲያን በሌላው በኩል ደግሞ ዓለም አቀፍ ክርስቲያን ነው፡፡ባልንጀራችሁን በክርስቲያንና በዓለም አቀፍ ክርስቲያን የሕይወት መንገድ መካከል በየት ስፍራ እንደሚገኝ ጠይቁ፡፡ በክርስቲያንና በዓለም አቀፍ ክርስቲያን መካከል ያለው ልዩነት ምን ይመስልሃል ብላችሁም ጠይቁ፡፡

**ማብራሪያ**: ስለ ዓለም አቀፍ ክርስቲያን የሕይወት መንገድ፡ በየትኛው አቅጣጫ ለመማርና ለማደግ ወይም ለማወቅ እንደሚፈልግ ጥያቄ አቅርቡ፡፡ ባልንጀራችሁ የሳበውን ነገር ለመግለጽ እንዲችል የተወሰነ ጊዜ መስጠት ይኖርባችኋል፡፡ ይህንን ፍላጎት መሠረት በማድረግ ፍለጋ የተባለውን ይህንን ጥናት፡ ከእናንተ ጋር እንዲያጠና ግብዣ አቅርቡ፡፡ ፍለጋ የተባለው ይህ ጥናት ሰዎች እነርሱ በሚፈልጉትም ሆነ በሌሎቹም አቅጣጫዎች ለማደግ እንዴት እንደሚረዳቸው ግለጹላቸው፡፡

**መደምደሚያ፡** ጥቂት ጊዜ ወስዳችሁ ጸልዩ፡፡

*መስኮቱን እንዴት ለሌሎች ማካፈል እንደምትችሉ ተለማመዱ፡፡*

# ተቀጽላ

## አንብቡ

ትምህርት 1

ትምህርት 2

ትምህርት 3

ትምህርት 4

ትምህርት 5

ትምህርት 6

ትምህርት 7

በትምህርቱ መጀመሪያ ላይ የሚገኙት የተጠቀሱት ምንባቦች በትራቭሊንግ ቲም ፈቃድ የተወሰዱ ናቸው፡፡
thetravelingteam.org

## ጸልዩ

ታሪኮቹ የተሰበሰቡት ከግሎባል ፕሬየር ዳይጀስት: globalprayerdigest.org
አኃዛዊ መረጃዎች የተገኙት ከጆሽዋ ፕሮጀክት: joshuaproject.net ነው፡፡

# ምስጋና

ልዩ ምስጋና ለመጀመሪዎቹ ጸሐፊዎችና የጽሑፉ አሰባሳቢዎች ለአንዲ ኬ. እና ለጆኤ ኤም. እንዲሁም ለአርታኢዎቹ ለክርስቲና ጄ እና ለቲቶ ኤች.

# ማስታወሻዎች

# አስተባባሪ

## መሆን




የእግዚአብሔርን ዓላማ **እንዲተገብሩት** ሌሎችም ጋብዟቸው፡፡

ሂዱ አስተባብሩን በመጠቀም ራሳችሁን አብዙ፡፡ በወንጌል ተደራሽ ያልሆኑ ሰዎች እንዲደረሱ ሌሎችን አነሳሱ፡፡

በmobilization.org/resources ላይ ይገኛል

ሂዱ አስተባብሩ እና አሰሳ በሚሽን ማዕከል የተዘጋጁ ጽሑፎች ናቸው፡፡ mobilization.org

# ፍለጋ

***XPLORE*** **IS A 7-LESSON STUDY TO HELP YOU DISCOVER:**

## የእግዚአብሔር ቃል

መጽሐፍ ቅዱስ በውስጡ ያለውን ሁሉ በአንድነት የሚያያይዝ የጋራ መሪ ሃሳብ አለው ወይስ የታላላቅ ታሪኮች ስብስብ ነው?

## የእግዚአብሔር ዓለም

ዛሬ በዓለም ላይ ከ7 ቢሊዮን የሚበልጡ ሰዎች እንዳሉ ታውቃላችሁ? እነማን ናቸው? እምነታቸውስ ምንድን ነው? ቤተክርስቲያን ምን እያደረገች ነው?

## የእግዚአብሔር ሥራ

እኛ የምንኖረው ለምን ዓላማ ነው? በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ ቦታችንን የምናገኘው እንዴት ነው? አንድ ሰው በእውነት ልዩነት ሊያመጣ ይችላል? እንዴት መጀመር እንችላለን?

CENTER FOR MISSION MOBILIZATION

ለተጨማሪ ትርጉሞች MOBILIZATION.ORG/XPLORE ን ይጎብኙ

ISBN 978-1-947468-04-7
90000>
9 781947 468047